# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ 81ኛ ዓመት ቁጥር 334 ነሐሴ 4 ቀን 2014 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!





# ‹‹በጸረ ሰላም ኃይሎች ላይ የተመዘገበው ድል በጸጥታ ኃይሉ የተሰራውን ሪፎርም ውጤት ያሳያል››

- ብርጋዴር ጀነራል ተስፋዬ ሃብተማርያም
የቀድሞ ሰራዊት አየር ወለድ አዛዥ

**ዘላለም ግዛው**



አዲስ አበባ:- በአሸባሪዎቹ አልሸባብ፣ ሕወሓትና ሸኔ ላይ የተመዘገበው ድል በጸጥታ ሃይሉ የተሰራውን ሪፎርም ውጤት እንደሚያሳይ የቀድሞ ሰራዊት አየር ወለድ አዛዥና የኅብረተሰባዊት ኢትዮጵያ ወደር የሌለው የጀግና ሜዳይ ተሸላሚ ብርጋዴር ጀነራል ተስፋዬ ሃብተማርያም ገለጹ፡፡

ብርጋዴር ጀነራል ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አልሸባብ፣ ሸኔና ሕወሓት ላይ የተገኘው ድል የመከላከያ ሰራዊትን የመዋቅር ጥንካሬ፣ በዘመናዊ ትጥቅ መደራጀቱን እና በብቃት መሰልጠኑን ያሳያል፡፡

የትኛውም አካል ቢመጣ አልሸባብን በመደምሰስ የደረሰው ሽንፈት እንደሚደገምበት ማስተማሪያ ጭምር ነው ያሉት ብርጋዴር ጀነራል ተስፋዬ፤ በአሸባሪዎች የተጠመደውን ማነቆ በአሸናፊነት መበጣጠስ የሚቻለው አንድነትንና ሕብረትን ማጠናከር ሲቻል እንደመሆኑ ድል ለመጎናጸፍ ጠንካራ ክንድ ሊኖር እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

‹‹ኢትዮጵያን የማዳከም ዘመቻ በዚህ ብቻ አያቆምም›› ያሉት ብርጋዴር ጀነራል ተስፋዬ፤ በሃይማኖት የማጋጨት፣ በጎሳ የማባላት፣ በዘር ከፋፍሎ ግጭት እንዲቀሰቀስ የማድረግ ሴራ የዚህ አካል መሆኑን በመገንዘብ ሕዝቡ ለአንድነቱና ለሉዐላዊነቱ መታገል ይኖርበታል ብለዋል፡፡

‹‹አሁን የተገኘው አንዱ ድል ነው፤ ፈተናው በጣም ብዙ እንደመሆኑ የሰራዊቱ ድልም ሊቀጥል ይገባዋል፤ ሕዝቡም አንድነቱን ማጠናከር አለበት›› ሲሉም ብርጋዴር ጀነራል ተስፋዬ ተናግረዋል፡፡

“በጸረ ሰላም ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል







# ባንኩ የብድር መጠኑን ወደ 22 ቢሊየን ብር ማሳደጉን አስታወቀ

- ከ300 በላይ ድርጅቶች ወደ ጤናማ ብድር እንዲመለሱ አድርጓል



ዶክተር ዮሃንስ አያሌው

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ከዚህ በፊት ይታቀድ የነበረውን 10 ቢሊየን ብር ከፍተኛ የብድር መጠን ወደ 22 ቢሊየን ብር ማሳደጉን አስታወቀ፡፡ ከ300 በላይ የሚሆኑ ድርጅቶችን ከተመላሽ ብድር ወደ ጤናማ ብድር እንዲመለሱ ማድረጉንም ጠቁሟል፡፡

የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ፕሬዚዳንት ዶክተር ዮሃንስ አያሌው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባንኩ የነበሩበትን ችግሮች በማስተካከል የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ሲሆን፤ ከዚህም አልፎ በአሁኑ ወቅት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በመሳብ በኢንዱስትሪው በኩል ከፍተኛ ስራ እያከናወነ ይገኛል፡፡

በኢንዱስትሪውና በግብርናው ዘርፍ ለአዳዲስ ፕሮጀክቶች እንዲጸድቅ በማድረግ ሰፊ ስራ ተሰርቷል ያሉት ዶክተር ዮሃንስ፤ ለኢንዱስትሪው ዘርፍ 14 በሊየን ብር በጀት መመደቡንና ለግብርናው ዘርፍም ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ

ባንኩ የብድር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# “ለሀገር በመቆም ኢትዮጵያን ካስቀደምን ማሸነፍ እንችላለን”

-አምባሳደር መስፍን ቸርነት
የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታ

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- እንደ አትሌቶቻችን ሁሉ ለሀገር በመቆም ኢትዮጵያን ካስቀደምን ማሸነፍ እንችላለን ሲሉ የባህልና ስፖርት ሚኒስትር ዴኤታው አምባሳደር መስፍን

“ለሀገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





‹‹ፍርድ ተዛብቶብኛል ፤ ሰበር ቅስሜን ሰብሮኛል›› ገጽ 6

እነክሪፕቶከረንሲ - የዲጂታል ግብይቱ ፈተናዎች ገጽ 9

# ለአምራች ኢንተርፕራይዞች ከ1 ነጥብ 6 ቢሊየን ብር በላይ ብድር ሊቀርብ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**


ፎቶ -ገበበ ገብሬ

አዲስ አበባ፡- በ2015 በጀት ዓመት ለአምራች ኢንተርፕራይዞች 1 ነጥብ 66 ቢሊየን ብር የስራ ማስኬጃ ብድር እንደሚቀርብ የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት አስታወቀ፡፡

ኢንተርፕራይዙ እንዳስታወቀው፤ የአምራች ኢንተርፕራይዞችን የፋይናንስ አቅርቦት ለማሳደግና ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ ታልሞ በተያዘው ዕቅድ በባንኮችና በማይክሮ ፋይናንስ አማካኝነት 1 ሺህ 591 ለሚሆኑ አምራች ኢንተርፕራይዞች 1 ነጥብ 66 ቢሊየን ብር የስራ ማስኬጃ ብድር ይሰራጫል።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ልማት ባንክና በሊዝ አክሲዮን ማህበራት አማካኝነት 1 ሺህ 430 ለሚሆኑ አምራች ኢንተርፕራይዞች 1 ነጥብ 6 ቢሊየን ብር የሚያወጡ ማምረቻ መሳሪያዎችን ለማቅረብም መታቀዱን ኢንተርፕራይዙ ይፋ አድርጓል።

ለአምራች ኢንተርፕራይዞቹ የሚቀርበው የስራ ማስኬጃ ብድር አቅርቦትና ማምረቻ መሳሪያዎች፣ አምራች ኢንተርፕራይዞች ተወዳዳሪ እንዲሆኑና ኤክስፖርትና ተኪ ምርቶች ላይ በብዛት መሰማራት እንዲችሉ ትልቅ እገዛ እንደሚኖረው ተጠቁሟል።

እንደ ኢንተርፕራይዙ መረጃ ከሆነ፤ በበጀት ዓመቱ ከክልል የዘርፉ ቢሮዎች፣ ከፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር የተጀመረውን ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከርና የሚያጋጥሙ ችግሮችን በፍጥነት በመፍታት ለአምራች ኢንተርፕራይዞቹ የስራ ማስኬጃ ብድርና የማሽን ሊዝ አቅርቦቱን ለማቀላጠፍ ታስቧል፡፡

በበጀት ዓመቱ በአምራች ኢንተርፕራይዝ ዘርፍ የስራ እድል ፈጠራ፣ የወጪ ንግድ ስራዎችና ተኪ ምርትን በሀገር ውስጥ የማምረት ስራዎች በልዩ ትኩረት እንደሚሰሩ እንደሚጠበቅ ከኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት የተገኘው መረጃ ያመላክታል፡፡


አቶ ዮናስ ታደሰ

# ኩባንያው በኢትዮጵያ ያለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት እየሰራ መሆኑን አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ያለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት ከዘርፉ ተዋናዮች ጋር በትብብር ለመሥራት እየተንቀሳቀሱ መሆኑን የኦቪድ ግሩፕ ኩባንያ አስታወቀ፡፡ ኩባንያው በኢትዮጵያ የግንባታ ኢንዱስትሪ ዘርፍ አዲስ ተስፋ መኖሩንም አመልክቷል፡፡

የ"ኦቪድ" ግሩፕ የግንባታ ኩባንያ ሥራ አስፈጻሚ ዮናስ ታደሰ ከኢዜአ ጋር በነበራቸው ቆይታ እንደተናገሩት፤ ኩባንያው እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ2013 በኢትዮጵያ ብሎም በአፍሪካ የሚታየውን ከፍተኛ የመኖሪያ ቤት ችግር ለመቅረፍ የተቋቋመ ነው፡፡

ኩባንያው ከተመሰረተ ጀምሮ አማራጭ የግንባታ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ውጤታማ ሥራ አከናውኗል ያሉት ዋና ስራ አስፈጻሚው፤ እስካሁን ባለው ሂደትም ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር በመተባበር በ18 ወራት ዘመናዊ የመኖሪያ መንደር ገንብቶ አጠናቋል ብለዋል።

አሁን በኢትዮጵያ ያለውን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመፍታት የዘርፉ ተዋናዮች በትብብር መሥራት አለባቸው ሲሉም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ትልቅ አገርና ሰፊ ሕዝብ ያላት እንደመሆኗ ሁሉም በትብብርና በቅንጅት ቢሰራ የበለጠ ውጤት ይገኛል። "ኦቪድ" ኩባንያም ይህንኑ በመረዳት በቀጣይ ከተለያዩ አጋሮች ጋር ትብብር እየፈጠረ የተሻለ ሥራ ለመሥራት መዘጋጀቱን ተናግረዋል።

ቀደም ባለው ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ግንባታዎች በተያዘላቸው ወጪና ጊዜ ሲጠናቀቁ እንደማይስተዋልም አንስተዋል።

"ኦቪድ" ኩባንያ ግን ወደ ግንባታው ዘርፍ ከተቀላቀለ ወዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ አዲስ ተስፋ መኖሩን በተግባር አሳይቷል ነው ያሉት።

ለአብነትም የድርጅቱ እህት ኩባንያ "ኦቪድ" ሪል ስቴት 12 ወለል ያለው ሕንጻ በሦስት ወራት ሰርቶ ማጠናቀቅ መቻሉን አንስተዋል።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም 10 ወለል ያለው ሕንጻ በ69 ቀናት ገንብተው ማጠናቀቃቸውን አንስተው፤ በዚህም በአጭር ጊዜ ውስጥ መኖሪያ ቤት ሰርቶ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ማሳየታቸውን ተናግረዋል።

በተጨማሪም ከፌዴራል ቤቶች ኮርፖሬሽን ጋር የተሰራው የገርጂ ሳይት የመኖሪያ መንደር ሕንጻዎቹ ከ1 እስከ 10 ወለሎች በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ መገንባታቸውን አንስተዋል።

በግንባታው ከተያዘው ጊዜ ውስጥ ስድስት ወራት የሚሆኑት የዝግጅት ሥራዎች የተሰሩባቸው እንደነበረም ገልጸዋል።

"ኦቪድ" በዘመናዊ ቴክኖሎጂ መታገዙ ብቻ ውጤታማ እንደማያደርግ በአግባቡ የተረዳ ኩባንያ መሆኑንም ሥራ አስፈጻሚው አንስተዋል።

ኩባንያቸው ከፕሮጀክቱ መሪዎች እስከ ሠራተኞች ድረስ በአገር ወዳድነት ስሜት በግንባታው ላይ የሚሳተፉ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

በተለይም የኩባንያው ሠራተኞች ፕሮጀክቶችን መገንባት አገር መገንባት መሆኑን እንዲረዱ ማስቻልና አስፈላጊውን ማበረታቻዎች እንደሚያገኙ እንደሚደረግም ተናግረዋል።

ኩባንያው ማህበራዊ ኃላፊነቱን ከመወጣት አንጻር በ2014 ዓ.ም ብቻ በተለያዩ አካባቢዎች ከ70 በላይ ቤቶች ግንባታና እድሳት ላይ መሳተፉንም አንስተዋል።

# ለመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ሕሙማን መርጃ ማዕከል የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ ቀረበ

## - የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለማዕከሉ ድጋፍ አድርጓል

**ፍቃዱ ዴሬሳ**

አዲስ አበባ፡- ለመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል በማንኛውም መልኩ የሚደረጉ ድጋፎች ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ጥሪ ቀረበ። የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ለመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል ድጋፍ አድርጓል።

የመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል አስተባባሪ አቶ ቃለወልድ ገረመው ድጋፉን አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት በማንኛውም መልኩ ለማዕከሉ የሚደረጉ ድጋፎች ለማዕከሉ ትልቅ ፋይዳ እንዳላቸው ጠቁመዋል።

ማዕከሉ አቅመ ደካማና ጧሪ የሌላቸውን ሰዎች እንዲሁም አዕምሮ ህሙማንን ከጎዳና በማንሳት ላለፉት አስር ዓመታት ሲረዳ የቆየ መሆኑን አንስተው፣ በአሁኑ ወቅት ማዕከሉ አዲስ አበባን ጨምሮ በሌሎች የሀገሪቱ አካባቢዎች ዘጠኝ ቅርንጫፎችን በመክፈት ለችግር የተጋለጡ ሰዎችን በየአካባቢያቸው እንዲረዱ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

በአዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ፣ ሀረር፣ ጎሬ፣ በኬ፣ ደሴ፣ አዳማ፣ ጋምቤላ እንዲሁም በሌሎች አካባቢዎች ከ7500 በላይ ተረጂዎችን በማቀፍ የሚረዳ ማዕከል ሲሆን ለወደፊቱም ወደ 20 ሺህ ለማድረስ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

አሁንም በርካታ የሚባሉ ሰዎች ጧሪ በማጣት እንዲሁም የአዕምሮ እክል ገጥሟቸው በጎዳናዎች ላይ የወደቁ ወገኖች እንዳሉ ያነሱት አስተባባሪው፣ በዚህ ክረምት ከ1500 በላይ ሰዎችን አንስቶ ለማስጠለል ማዕከሉ እየሰራ መሆኑን ገልፀዋል።


ፎቶ -ፀሐይ ንጉሤ

አቶ ቃለወልድ ገረመው

በመሆኑም የማዕከሉ አገልግሎት በአብዛኛው በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ሰጪዎች የሚንቀሳቀስ በመሆኑ በዚህ የክረምት ወቅት ደጋፊ የሚሹ ወገኖቻችን ይበልጥ ለከፋ አደጋ የሚጋለጡ በመሆናቸው በዚህ ረገድ ወጣቱ ርብርብ እንዲያደርግና የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊወጣ እንደሚገባ ጠቅሰዋል።

በጎ አድራጎት ስራ ላይ የተሰማሩ ግለሰቦችና ቡድኖች ለማዕከሉ የተለያየ ድጋፍ በማድረግ ለዚህ ያበቁ ቢሆንም አሁንም ቀጣይ ባለው መልኩ በማንኛውም ዘርፍ በሙያም ሆነ በቁሳቀስ እንዲሁም በገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እንደሚገባም አቶ ቃለወልድ ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅትም በስፍራው በመገኘት የማገዶ እንጨት ማስረከቡና ማዕከሉን መጎብኘቱ የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑን ጠቅሰው፣ ለሌሎች ተቋማት አርአያ የሚሆን ተግባር መሆኑን ተናግረዋል።

ማንኛውም ተቋም እንዲሁም ግለሰብና ቡድን በምንም መልኩ የሚያደርገው ድጋፍ ለመቄዶንያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል የሚጠቅም መሆኑን ተገንዝቦ ከማዕከሉ ጎን እንዲቆም ጥሪ አስተላልፈዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ተጠባባቂ ኃላፊ ወ/ሮ ብርሃኔ ደመቀ በበኩላቸው፤ መቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል በርካታ ድጋፍ የሚያስፈልገው ማዕከል በመሆኑ ድርጅቱ አቅም በፈቀደ መጠን አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶችን እንዲሁም ሌሎች ድጋፎችን ያደርጋል ብለዋል።

ሁሉም ማህበረሰብ በመቄዶንያ የአረጋውያንና አዕምሮ ህሙማን መርጃ ማዕከል በመገኘት ተረጂዎች በምን ሁኔታ ውስጥ እንዳሉ በመጎብኘት በሚያስፈልገውና አቅም በፈቀደው መልኩ የበኩሉን ድጋፍ እንዲያደርግም ጥሪ አቅርበዋል።

# በአዲስ አበባ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ከሦስት ቢሊየን ብር በላይ ማዳን ተችሏል

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ በጀት ዓመት በአዲስ አበባ በበጎ ፍቃድ አገልግሎት ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ ማዳን መቻሉን የአዲስ አበባ የህዝብ ተሳትፎ ማስተባበሪያና በጎ ፍቃድ አገልግሎት ኮሚሽን አስታወቀ። በኑሮ ውድነቱ ምክንያት ለከፋ ችግር ለተጋለጡ ወገኖች ዘላቂ መፍትሄ ለማበጀት ከሚደረገው ስራ ጎን ለጎን የማዕድ ማጋራት ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ተጠቁሟል።

ኮሚሽነሩ አቶ አስፋው ተክሌ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት አስተያየት፣ በከተማው ነዋሪዎች ዘንድ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ በተለያዩ ዘርፎች በተሰራው ሥራ ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ የመንግስት ወጪ ማዳን ተችሏል።

በከተማችን እንደ አለም ትልቁ ፈተና የሆነው የኑሮ ውድነት ከፍተኛ ጫና ያረፈባቸውን ወገኖች ለመርዳት የማዕድ ማጋራት ሥራ እየተከናወነ ነው ያሉት ኮሚሽነሩ፤ ነገር ግን ማዕድ ማጋራት ብቻውን ዘላቂ መፍትሄ ስለማይሆን መንግስት ዘላቂ መፍትሄ ላይ በትኩረት እየሰራ ይገኛል ብለዋል።

ማዕድ ማጋራት ባደጉት አገራት ሳይቀር የሚሰራ በጎ ተግባር ቢሆንም በከተማው ሰርተው መብላት እየቻሉ የሥራ እድል በማጣታቸው ምክንያት ተረጂ የሆኑ ዜጎች የተረጂነት ስሜት እንዳያዳብሩ መሥራት የሚችሉትን በመለየት ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን የስራ እድል ማመቻቸት ላይ እየተሰራ እንደሆነም ኮሚሽነሩ ጠቁመዋል።

ነገር ግን መሥራት የማይችሉ አቅመ ደካሞች በቋሚነት



**አቶ አስፋው ተክሌ**

ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ላይ መንግስት ከባለሀብቶች ጋር በመተባበር እየሰራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከግንቦት እስከ ሰኔ መጨረሻ ብቻ ለ407 ሺህ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው የከተማው ነዋሪዎች ማዕድ ማጋራት መቻሉን ያነሱት ኮሚሽነሩ፣ በተጨማሪም በቀጣዩ የእሬቻና የመስቀል ክብረ በዓል ላይ በየቦታው የእንኳን ደህና መጣችሁ አቀበባል በማዘጋጀት ከተለያዩ አካባቢ ወደ አዲስ አበባ ለሚመጡ የበዓሉ ታዳሚዎች ማዕድ ለማጋራት ማቀዳቸውንም ጠቅሰዋል።

እንደ ከተማው መስተዳድር ለበጎ ፍቃድ የተለዩ ዘርፎች የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ ማዕድ ማጋራት፣ የደም ልገሳ፣ አረንጓዴ አሻራ፣ የከተማ ጽዳት፣ ነጻ የህክምና አገልግሎትና የማጠናከሪያ ትምህርት መስጠት መሆናቸውን የተናገሩት አቶ አስፋው፤ የክረምት በጎ ፍቃድ አገልግሎት ቢሆንም መርሀ ግብሩ እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚቀጥልም አመልክተዋል።

እስካሁን 3 ሺህ 88 የአቅመ ደካሞችና የአገር ባለውለታዎች ቤቶች በአማካይ ለእያንዳንዳቸው 400ሺህ ብር ወጪ በማድረግ ማደስ መቻሉን የጠቀሱት ኮሚሽነሩ፣ ስሙ እድሳት ይባል እንጂ ከባለሀብቶችና ከህዝቡ እርዳታ በማሰባሰብ ሙሉ በሙሉ አዲስ ቤቶች ተገንብተው ከቤት ቁሳቁስ ጭምር ለባለቤቶቹ ርክክብ ማድረጋቸውን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ መልኩ በዘንድሮው አረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብሩ በከተማዋ 13 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ እስካሁን ስምንት ሚሊዮን ችግኝ መተከሉንና የቀሩትን ደግሞ ቀጣይ ቀናት ለመትከል እቅድ መያዙን የገለጹት ኮሚሽነሩ፣ በመንግስትና በግል የጤና ተቋማት በጎ ፍቃደኛ የጤና ባለሙያዎችን በማሳተፍ ለ2 ሺህ 578 የከተማዋ ነዋሪዎች ነጻ የህክምና አገልግሎት መሰጠቱን አንስተዋል።

የደም እጥረት ለመቅረፍ እስካሁን ከ9 ሺህ ዩኒት ደም በላይ መሰብሰቡንና የትራፊክ አደጋን ለመቀነስ በ130 አደባባዮች ላይ ከ3 ሺህ በላይ በጎ ፍቃደኞች ማሰማራታቸውን የገለጹት አቶ አስፋው፣ በተለያዩ ክልሎችም በተለያዩ የሙያ ዘርፍ አገልግሎት የሚሰጡ 1 ሺህ 200 በጎ ፈቃደኛ ወጣቶች መሰማራታቸውን ጠቁመዋል።

# የሲሚንቶ ከረጢትን በአገር ውስጥ ምርት መተካት መቻሉ ተጠቆመ

**ፀጋዬ ፐሳሁን**

አዲስ አበባ፡- ከውጭ ይገባ የነበረው የሲሚንቶ ከረጢት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በአገር ውስጥ ምርት መተካት መቻሉን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ገለፀ።

የኮርፖሬሽኑ የኦፐሬሽን ዘርፍ ምክትል ዋና ዳሬክተር አቶ ሽፈራው ሰለሞን በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች ከውጭ ያስገቡት የነበረውን የሲሚንቶ ከረጢት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ማስቀረት ተችሏል።

ዘርፉ ለኢኮኖሚው እድገት የራሱን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት የሚያስችሉ ስራዎች እየተሰሩ ነው ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርቶች የኤክስፖርትና የገቢ አቅምን ሊያሳድግ የሚያስችል ስራ እየተሰራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ሽፈራው ገለጻ፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች መቋቋም አላማ ኤክስፖርትን ማሳደግ፣ ገቢ ምርቶችን መተካትና የምንዛሬ አቅምን ማሳደግ ነው። በፊት ፓርኮች ትኩረት የሚያደርጉት ማኑፋክቸሪግ፣ ውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት መሳብና ገቢ ምርቶችን መተካት ነበር። በአሁኑ ወቅት ግን የቢዝነስ እይታ ለውጦች እየተደረጉ ነው።

አሁን በዘርፉ የሎጂስቲክስ፣ የስልጠና፣ የመጋዘን እና ሌሎች አገልግሎቶችን አካቶ እየተሰራ እንደሆነም አቶ ሽፈራው ጠቁመዋል።

የቢዝነስ ልውውጥ እንዲኖር መደረጉ ፓርኮች ውጤታማ እንዲሆኑ እንደሚያደርግ ታምኖበታል ያሉት አቶ ሽፈራው፤ አሁን ያሉት 13 ፓርኮች ብቻ በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ትልቅ እምርታዊ ለውጥ ስለማያመጡ አዳዲስ ፓርኮችን መጨመር አስፈላጊ መሆኑን አስረድተዋል።

አሁን ያለው የፀጥታ ሁኔታ ቀጣይነት ካለው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ወደ ቀደመ ስራቸው ተመልሰው ውጤታማ ይሆናሉ። በአጠቃላይ ግን ውጤታማነቱ የሚረጋገጠው የሚመለከታቸው አካላት ተሳታፊ ሲሆኑ ነው ብለዋል።

በሌላ በኩል የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው በስፋት ኢንቨስት እንዲያደርጉ ኮርፖሬሽኑ ጥሪ አቅርቧል። የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ገብተው ኢንቨስት ለማድረግ የቢዝነስ ፕሮፖዛሎችን አስገብተው በእንቅስቃሴ ላይ መሆናውንና ኮርፖሬሽኑ ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለሚያለሙ የአገር ውስጥ ባለሀብቶች ተገቢውን አገልግሎት ለመስጠትም ዝግጁ እንደሆነ ዳይሬክተሩ ተናግረዋል።

በአሁኑ ወቅት ከ15 በላይ የውጭና የአገር ውስጥ ባለሀብቶች በተለያዩ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለመሥራት እንቅስቃሴ ላይ ናቸው ያሉት አቶ ሽፈራው፤ የቢዝነስ ፕሮፖዛላቸው ተገምግሞ ውሳኔ እንዲሚሰጥባቸውም አስረድተዋል።

ባለፉት ሁለት አመታት በነበሩት ኮሮናና የፀጥታ ችግር የኢንቨስትመንት ፍሰቱ ተቀዛቅዞ ቢቆይም አሁን ግን በተሻለ ሁኔታ እየተነቃቃ እንደሆነም ተጠቁሟል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ80 ሺህ በላይ ለሆኑ ሰዎች የስራ ዕድል የተፈጠረ ሲሆን፤ ከዚህ ውስጥ ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ሴቶችና ወጣቶች እንደሆኑ ኃላፊው ጠቁመዋል። ከዚህ ውጪም ከ300 መቶ ሺህ በላይ ዜጎች በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ እንደሆኑም ተናግረዋል።




# ኤክስፖ 2022 ለዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተገለጸ

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የአፍሪካ የቴክኖሎጂ ኤክስፖ 2022 በአዲስ አበባ ለማካሄድ መታቀዱ የአፍሪካን ነጻ የንግድ ቀጣናን እውን ከማድረጉም ባሻገር ለዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር አምባሳደር ዲና ሙፍቲ አስታወቁ፡፡

በመጪው ጳጉሜን ወር የሚካሄደውን ኢትዮጵያ የአፍሪካ የቴክኖሎጂ ኤክስፖ 2022 አስመልክቶ ጋዜጣዊ መግለጫ በተሰጠበት ወቅት የተገኙት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ዳይሬክተር አምባሳደር ዲና ሙፍቲ እንደገለጹት፤ ይህ የቴክኖሎጂ ኤክስፖ በአዲስ አበባ መካሄዱ ለኢትዮጵያ ተስማሚ ቴክኖሎጂን ከመምረጥ ጀምሮ የቴክኖሎጂ ዝውውር ለማምጣት ይረዳል፡፡ እንዲሁም በአገር ገጽታ ግንባታና ለኢኮኖሚ ልማት ትልቅ ፋይዳ ይኖረዋል፡፡

የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ለኢንቨስትመንት መሳለጥና ለንግድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው ያሉት አምባሳደሩ፤ ለአንድ አገር ሰላምና ጸጥታ መከበርም የጎላ ሚና አለው ብለዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር ለዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት የሚያበረክተው ፋይዳ ቀላል የሚባል አይደለም ያሉት አምባሳር ዲና፣ ከዚህ አንጻር ይህ መድረክ አገራችንን ወደፊት ለማሳደግና የአገራችንን ሰላምና ጸጥታ ለመገንባት ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ዲና ገለጻ፤ በኤክስፖው የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተለያየ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋሉ፤ በተለይ የቴክኖሎጂ ባለቤቶች፣ የንግዱ ማሕበረሰብ አባላትና ሌሎች ተቋማት ሁሉ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖራቸው ገልጸዋል፡፡

ኤክስፖውን በኢትዮጵያ ለማካሄድ መታቀዱ ጠቀሜታው በአፍሪካና በአለም አቀፍ ደረጃ የጎላ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ከቴክኖሎጂ ሽግግር ባሻገር የገጽታ ግንባታና ንግድን የማሳለጥ ቱሩፋት እንደሚኖረውም ጠቁመዋል፡፡

እንደ አምባሳደር ዲና ገለጻ፤ በአፍሪካና በአለም ያሉ ስመጥር የቴክኖሎጂ ባለቤቶች በኢትዮጵያ እንዲሳተፉ መደረጉ ነጻ የአፍሪካ የንግድ ቀጣና ለማምጣት ያግዛል፡ ፡ ይህ ደግሞ በአፍሪካ ሕብረትና በመሪዎች ደረጃ ብዙ የታሰበበት በመሆኑ ምኞቱን እውን ያደርጋል፡፡

ኤክስፖው የንግድ ቀጣናውን በአፍሪካና በአለም ደረጃ ለማስፋፋት የሚረዳ በመሆኑ ጠቀሜታውን በማጉላት ለሕብረተሰቡ ማሳወቅና መሳተፍ የሚችሉትም እንዲሳተፉ ማድረግ አስፈላጊ ነው ሲሉም አስረድተዋል፡፡

የጆርካ ኤቨንት ማርኬቲንግና ኮሙኒኬሽን ኃላፊ አቶ ሳምሶን ኃይለእየሱስ በበኩላቸው፤ ኤክስፖ 2022 በአዲስ አበባ ከጳጉሜን 2 እስከ 4 የሚካሄድ ሲሆን በጆርካ ኤቨንት እና ATX በጋራ በመሆን የተዘጋጀ ነው።

ኤክስፖው ዘመኑ ያፈራቸውን ቴክኖሎጂዎች ለማስተዋወቅ ያለመ ሲሆን፤ ምርቶችን ከማስተዋወቅ ባሻገር በቴክኖሎጂ ዙሪያ አፍሪካንና የሌላውን አለም የንግድ ትስስር ለማስተዋወቅ የተዘጋጀ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

በኤክስፖው ከአፍሪካ፣ ከአውሮፓ፣ከእስያ፣ ከሰሜን አሜሪካ አንጋፋ የቴክኖሎጂ ኩባንያዎች ይሳተፉሉ ያሉት ኃላፊው፤ ከ45 ሺህ በላይ ጐብኚዎችና ገዥዎች የአፍሪካ ቴክ ኤክስፖን ይጎበኙታል ተብሎ እንደሚጠበቅም ተናግረዋል፡፡

ኤግዚቢሽኑን ለየት የሚያደርገው በሶላር ቴክኖሎጂ፣ በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች፣ በዲጂታል ክፍያ ስርአቶች፣ በቴሌኮሙኒኬሽን የባንክ ስራዎችና በኢንሹራንስ ላይ ልዩ ትኩረት የሚሰጥበት በመሆኑ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ኃላፊው ገለጻ፤ የአፍሪካ ቴክ ኤክስፖ ትልቅ የግብይትና የሽያጭ እድሎችን ያመቻቻል፡፡ አፍሪካ ለጀመረችው ነፃ የንግድ ቀጣና እውን መሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

ኤክስፖው ወደፊት በተለያዩ የአፍሪካ ሃገራት እንደሚዘጋጅ የጠቆሙት ኃላፊው፤ የአፍሪካ የባንክ ዘርፍና ኤሌክትሮኒክ ክፍያ ስርዓት ስትራቴጂ፣ የአፍሪካ ቴሌኮም ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣ ስራ ፈጠራ እድሎች በአፍሪካ ቴክኖሎጂ መድረክና በሌሎችም ኢንቨስትመንቶች ላይ በሚደረገው ግስጋሴዎች ላይ ሲምፖዚየሞች ይከናወናሉ ብለዋል፡፡

# ክልሉ ከ64 ሺህ ቶን በላይ የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረቡን አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2014 የምርት ዘመን ከ64 ሺህ ቶን በላይ የታጠበና ያልታጠበ የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረቡን የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል አስታወቀ።

የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ ይህን የገለጹት የክልሉ ምክር ቤት ቦንጋ ከተማ እያካሄደ ባለው ስድስተኛ ዙር አንደኛ የሥራ ዘመን ሁለተኛ መደበኛ ጉባኤ ላይ የ2014 በጀት ዓመት የተግባር አፈጻጸም ሪፖርት ሲያቀርቡ ነው፡፡

ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ በዚሁ ጊዜ እንደገለጹት፤ በ2014 የምርት ዘመን 221 ነጥብ 7 ሺህ ቶን አጠቃላይ የቡና ምርት ለመሰብሰብ ታቅዶ 239 ነጥብ 7 ሺህ ቶን የቡና ምርት መሰብሰብ ተችሏል።

ከዚህም ምርት ውስጥ 61 ሺህ 864 ቶን የቡና ምርት ለገበያ ለማቅረብ ታቅዶ ከዕቅድ በላይ 64 ሺህ 470 ቶን ጥራቱን የጠበቀ የቡና ምርት ለማዕከላዊ ገበያ ማቅረብ ተችሏል ብለዋል።

ለማዕከላዊ ገበያ ከቀረበው የቡና ምርት ከ20 ሺህ ቶን በላይ ምርት የታጠበ መሆኑን አብራርተዋል።

ሕገ ወጥ የግብይት እንቅስቃሴን ለመከላከል በተደረገው ጥረት ከ170 ቶን በላይ ሕገ ወጥ ቡና በመያዝ ከ15 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ገቢ መገኘቱን ገልጸዋል።

በክልሉ በ2013 ዓ.ም የነበረውን 541 ሺህ ሄክታር የቡና ማሳ ሽፋን ወደ 559 ሄክታር ማሳደግ መቻሉ ተጠቅሷል።

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል ምክር ቤት ጉባኤውን ማካሄድ የጀመረው ትናንት ሲሆን፤ ምክር ቤቱ በቦንጋ ከተማ እያደረገ በሚገኘው ጉባኤ የክልሉ ምክር ቤት፣ የአስፈጻሚ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ዋና ኦዲት መስሪያ ቤት የ2014 በጀት ዓመት አፈጻጸም እና የ2015 እቅድ ላይ መክሯል።



ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ

ለሁለት ቀናት በሚደረገው የምክር ቤቱ ጉባኤ ላይ የ2015 የሥራ ዘመን እቅዶች ማስፈጸሚያ በጀት ቀርቦ ውይይት እንደሚደረግበት ከወጣው መርሐ ግብር ማወቅ ተችሏል። በጉባኤው የተለያዩ አዋጆችና ሹመቶች ቀርበው ይጸድቃሉ ተብሎ ይጠበቃል።

ክልሉ ከተመሠረተበት ህዳር 2014 ዓ.ም ጀምሮ የልማት፣ የመልካም አስተዳደርና የፍትህ ጥያቄዎችን ለመመለስ ውጤት የታየበት ስራ ማከናወኑን የክልሉ ምክትል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ኢንጂነር ነጋሽ ዋጌሾ ሐምሌ 30 ቀን 2014 ዓ.ም መግለጻቸው ይታወሳል።

## ባንኩ የብድር...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እንደሆነ አብራርተዋል፡፡

በዚህም መሰረት ባንኩ ከዚህ ቀደም ይሰጥ የነበረውን አስር ቢሊየን የማይበልጥ ከፍተኛ የብድር መጠን በአሁኑ ወቅት ወደ 22 ቢሊየን ብር በማሳደግ አገልግሎት አድማሱን ለማስፋት እየሰራ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

እንደ ዶክተር ዮሃንስ ገለጻ፤ ከዚህ በፊት በከፍተኛ ኢንቨስትመንት የተቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች በተበላሸ ብድር ውስጥ ገብተው ስራ አቁመው ፋይናንስ የማያገኙበትና የነበሯቸውን ሰራተኞች በትነው ችግር ውስጥ የነበሩበት ሁኔታ ነበር፡፡ ግብር በመክፈል በኩልም ሁሉም ኪሳራ ውስጥ ስለነበሩ ምንም አይነት ግብር ለመንግስት የማይከፍሉበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡

ዶክተር ዮሃንስ እንደተናገሩት፤ ባንኩ በትኩረት በሰራው ስራ ከ300 በላይ የሚሆኑ ድርጅቶች ከተበላሸ ብድር ወደ ጤናማ ብድር እንዲመለሱ እንዲሁም ከ10 አመት በላይ ችግር የነበረባቸው ስድስት ቢሊየን ካፒታል ያላቸው አራት ኢንዱስሪዎች ከችግራቸው ወጥተው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

ከነዚህ ኢንዱስትሪዎችም ሶስቱ የቱርክ ኩባያዎች እንደሆኑ የተናገሩት ዶክተር ዮሃንስ፤ አራቱም ኢንዱስትሪዎች ከባለፈው አመት ሰኔ ጀምሮ በአንድ አመት ውስጥ የተቀየሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል፡፡ ኢንዱስትሪዎቹ የበላሸባቸውን ብድር ሙሉ በሙሉ ከፍለው ወደ ጤናማ የስራ እንቅስቃሴ መግባታቸውንም ተናግረዋል፡፡

እንደ ፕሬዚዳንቱ ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ልማት ባንክ ለአነስተኛና መካከለኛ ዘርፍ በሰጠው ትኩረት ከ35 ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የቢዝነስ ፈጠራ ስልጠና የሰጠ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ 28 ሺ የሚሆኑት ለሰርቲፊኬት ብቁ ሆነዋል፡፡ የባንኩን መስፈርት አሟልተው ወደ ቢዝነስ ለሚገቡ ስራ ፈጣሪ ኢንተርፕራይዞች ከ10 ቢሊየን ብር በላይ ብድር አመቻችቷል፡፡

ዶክተር ዮሃንስ፤ ባንኩ በተጠናቀቀው 2014 በጀት አመት የትግራይ ክልልን ሳይጨምር ከሰጠው ብድር 10 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር እንደሰበሰበና የተበላሸ ብድር ደረጃን ወደ 17 በመቶ ማውረድ እንደተቻለም ተናግረዋል፡፡

ባንኩ የገጠመውን ችግር ለማካካስ ፈጣን ለውጦችን ማድረግ በመቻሉ በ2013 በጀት አመት የነበረውን የተበላሸ የብድር ደረጃ ከነበረበት 15 ቢሊየን ብር በበጀት አመቱ ወደ 9 ቢሊየን ብር ዝቅ ማድረግ ተችሏል። 11 ቢሊየን ብር የሚጠጋ ገንዘብ ከብድር መሰብሰቡንም ዶክተር ዮሃንስ አያሌው ተናግረዋል፡፡

## “ለሀገር በመቆም....

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ቸርነት ገለጹ፡፡ አምባሳደሩ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በ19ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ባስመዘገቡት ድል የተሰማቸውን ደስታ በመግለፅ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብም የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

አምባሳደር መስፍን ቸርነት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ መላው የሀገራችን ህዝብ ከጥቃቅን ጉዳይ ወጥቶ ቅድሚያ ለሀገር በመስጠት ለሀገሩ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ ማበርከት አለበት፡፡

ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ከግለኝነት አስተሳሰብ ወጥተው ለሀገር ሰንደቅ ቅድሚያ በመስጠት ያመጡት አንፀባራቂ ድል በሁሉም ዘርፍ ለሚገኝ ዜጋ አስተማሪ እንደሆነም አምባሳደር መስፍን ጠቁመዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ደኤታው ንግግር፤ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ሀገርና ህዝብን፣ የሰንደቅ ፍቅርን በማስቀደም የሀገራቸውን ሰንደቅ በዓለም አደባባዮች ላይ ከፍ በማድረግ ለሀገራቸው የከፈሉት ውድ ዋጋም የሚያስመሰግናቸው ሲሆን መላው ኢትዮጵያዊም ለአትሌቶቹ የሚገባቸውን ክብር ሊሰጥ ይገባዋል፡፡

አትሌቶች በተባበረ ክንድ እንዲሁም በጠነከረ ጉልበት ያስገኙትን ድል በሁሉም የስራ መስክ በመድገም እኔ ለእኔ ብቻ ማለትን በመተው እኛ ለእኛ ማለት እንደሚያሻ ያመላከቱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ሁሉም በየተሰማራበት የስራ ዘርፍ ሊጀግን እንደሚገባው ተናግረዋል፡፡

ከእኔነት ወጥቶ ለጋራ ህልውና ለሀገር በመቆም ኢትዮጵያን ካስቀደምን ማሸነፍ እንችላለን ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በዘርፉ ወጣቶችን ማፍራት ላይ ስራዎች መከናወናቸውን በማመላከት በቀጣይም ጠንክሮ መስራት እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

ስፖርት በየትኛውም ሀገር ላይ ሰላምን፣ ፍቅርን፣ የሀገር እድገትና የገፅታ ግንባታ ስራን እንደሚከውን የጠቆሙት አምባሳደር መስፍን፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሰሩትን ፈርጀ ብዙ መልካም ተግባራት ማስተዋወቅ ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚጫወትም ነው የገለፁት፡፡

መንግስት ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ላይ ልዩ ትኩረት መስጠቱን ያመላከቱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ከሰባ በመቶ በላይ ወጣት ባላት ሀገር ላይ ለስፖርት ትኩረት መሰጠቱ ዘርፉን ለብዙዎች የሚተርፍ እንደሚያደርገው በመግለፅ፤ በቀጣይ ዘርፉን በማልማት ስፖርትን ለልማት ማዋል ላይ ለመስራት ዝግጅቶች መጠናቀቃቸውንም ነው ያመላከቱት፡፡

በኮሎምቢያ ካሊ ከሀምሌ 25 እስከ 30 በተደረገው 19ኛው የዓለም ከ20 ዓመት በታች አትሌቲክስ ሻምፒዮና ኢትዮጵያ 6 ወርቅ፣ 5 ብር እና አንድ የነሃስ በአጠቃላይ 12 ሜዳልያዎችን በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ ከአለም ደግሞ 3ኛ ደረጃን በመያዝ ውድድሩን ማጠናቀቋ የሚታወቅ ነው፡፡

## ‹‹በጸረ ሰላም ኃይሎች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በጎሳና በሃይማኖት መከፋፈሉ እንደማይጠቅም መገንዘብ ይገባል። በጎሳ፣ በብሄር፣ በሃይማኖት መከፋፈል ውድቀትን እንጂ አንድነትን እንደማያመጣ፣ ድልንም እንደማያጎናጽፍ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊገነዘብ ይገባል ሲሉም ተናግረዋል።

አሸባሪዎቹ ሕወሓት፣ ሸኔ እና አልሸባብ የውጭ ሃይሎችን ተልዕኮ በመቀበል ኢትዮጵያን ለመበታተን እየሰሩ እንደሚገኙ በመጥቀስም፤ ኢትዮጵያን ለማዳከም የሚያደርጉት እንቅስቃሴ የግድቡን ግንባታ የማስተጓጎል ዓላማም እንዳለው ጠቁመዋል።

ብርጋዴር ጄኔራል ተስፋዬ እንደገለጹት፤ ጠላቶቻችን አሸባሪዎችን እያስታጠቁ፣ እያሰለጠኑ፣ በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ እየደገፉ ልማትን ለማደናቀፍና ሰላም ለማናጋት ይሰራሉ፤ የሕዳሴ ግድብ ግንባታን ለማደናቀፍ የሚፈልጉ የውጭ ሃይሎችም የጠላት ሃይሎች ፍላጎት እንዲሳካ ይደግፋሉ።

የአሸባሪ ቡድኖቹ ዋና አላማ የተበጣጠሰች፣ ደካማ እና የተከፋፈለች አገር መፍጠር ነው ያሉት ጀነራል ተስፋዬ፤ በሃይማኖት ሰበብ ግጭት እንዲነሳ የመቀስቀስ ፍላጎትም አለ ብለዋል። ይህንን ለማምከን የውስጥ አንድነትን ማጠናከር እንደሚያስፈልግም ነው የተናገሩት። ሰራዊቱ ብቻውን አገር ማስከበር ስለማይችል ዜጎች አካባቢያቸውን መጠበቅ እንዳለባቸውም አሳስበዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ከሽብር ሃይሎች ጀርባ የሚንቀሳቀሱት የውጭ ሃይሎች ዓላማ እና ፍላጎታቸውን የሚያስፈጽምላቸው መንግስት እንዲመሰረት ይፈልጋሉ። እነዚህ ሃይሎች እነርሱ ያወጡትን መመሪያ እና ትእዛዝ የማይቀበል መንግስት ደግሞ ለመጣል ይረባረባሉ።

“አሸናፊም ሆነ ተሸናፊ ወገን ከጦርነት የሚያተርፉት ጉዳት ነው። ማንም ወደጦርነት መግባት አይፈልግም። ነገር ግን ሽሽተን የትም መድረስ ስለማንችል የግድ ራስን ማስከበር ይኖርብናል። ለዚህም ሰራዊቱን ማጠናከር ወሳኝ ነው” ሲሉም ተናግረዋል።

የአገር ዳር ድንበርን የማስጠበቅ ጉዳይ የሰራዊቱ ብቻ ሊሆን እንደማይገባ የጠቆሙት ጀነራሉ፤ ኢትዮጵያውያን የአገር አንድነትን የማስከበር ግዴታቸውን ሊወጡ እንደሚገባ፣ ወጣቱም ወደ ሰራዊቱ በመቀላቀል ለሉዓላዊነቱና ለአንድነቱ መታገል እንዳለበት አመልክተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሰላምን ለማስፈን በሚደረገው ጥረት የዜጎች ተሳትፎ የማይተካ ነው!

ሰላም የሁሉም ነገር መሰረት ነው። ሰርቶ ለመኖር፤ በሀገር ለመኩራት፤ ወልዶ ለመሳም፤ ወጥቶ ለመግባት ሰላም በእጅጉ ያስፈልጋል። ሰላም በሌለበት ነግዶ ማትረፍ፤ተምሮ ለቁም ነገር መብቃት ፤ በዜግነት መኩራትና የዕለት ተዕለት ኑሮን መምራት አዳጋች ነው። በአጠቃላይ ያለ ሰላም ሕይወት የምድር ሲኦል ናት።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላም ወዳድ ሕዝብ ነው። ለዘመናት አብሮ ተከባብሮ በመኖርና የሰላም ተምሳሌት በመሆን በአርአያነት ሲጠቀስ የኖረ ሕዝብ ነው። ከኢትዮጵያውያን ዘመን ተሻጋሪ አኩሪ መገለጫዎች መካከል የብሔር፣ የእምነት፣ የቋንቋ፣ የባህልና ሌሎች ልዩነቶችን ዕውቅና በመስጠት ተሳስቦና ተከባብሮ መኖር ትልቁ እሴት ነው። ከዚህም አልፎ የውጭ ሀገር ዜጎች ምንም አይነት የባዳነት ስሜት ሳይሰማቸው እንደሀገራቸው እንዲኖሩ የሚፈቅድ ድንቅ ሕዝብ ነው።

ሆኖም የዘመን ጉድ የሆኑ አንዳንድ ፖለቲከኞች ነን ባዮች የዚህን ኩሩ ሕዝብ የዘመናት እሴቶች ለመናድ ሲሯሯጡ ይታያሉ። ልዩነቶችን ጌጡ አድርጎ የኖረውን ሕዝብ እርስ በእራሱ እንዳይተማመን እና እንዲጋጭ የሚያደርጉ ትርክቶችን በመፍጠር በሀገሪቱ ሁከትና ብጥብጥ እንዲነግስ ያለመታከት በመስራት ላይ ይገኛሉ። ብዙዎቹ ፖለቲከኞች የራሳቸው አንድም ሃሳብ ሳይዙ በተላላኪነትና በባንዳነት ተፈርጀው ለብጣሽ ዶላር ሲሉ አንዱን ብሄር በሌላው ላይ በማስነሳት ሀገርን ለማፍረስ ቆርጠው ተነስተዋል።

በዚህም የዜጎችን በሰላም የመኖር መብት አደጋ ላይ የጣሉና የአገርን ሰላምና ደሕንነት የሚያውኩ ሙከራዎችም ተከስተዋል። በወለጋ፤ በሶማሌ፤ በሰሜን ሸዋ፤ በመተከልና በደቡብ ክልል አንዳንድ አካባቢዎች በነዚሁ የጥፋት ኃይሎች አማካኝነት በርካታ ዜጎች ተገድለዋል፤ ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል፤ ለአስከፊ ሕይወትም ተጋልጠዋል።

በአሸባሪው ሕወሓት አማካኝነት በትግራይ ክልል ተቀስቅሶ አጎራባች ወደሆኑት አማራ እና አፋር ክልሎች ተሸጋግሮ የነበረው የሰሜን ኢትዮጵያው ጦርነት በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ከቀያቸው ማፈናቀሉ ይታወቃል። ይህንን ጦርነት ተከትሎ በትግራይ፣ በአማራ እና በአፋር ክልሎች በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ተፈናቅለዋል።

ኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሀብቷን እንዳታለማ ዘወትር እንቅፋት የሚሆኑ የውጭ ኃይሎች ከውስጥ ተላላኪዎች ጋር በመሆን በርካታ የጥፋት ድግሶችን ሲደግሱ ኖረዋል። አሸባሪዎቹ የሕወሓትና የሸኔ ኃይሎች እንዲሁም የጉሙዝ ታጣቂዎች ከአልሻባብና ከውጭ ጠላቶች ጋር በማበር ሀገሪቱን ለማመስ በቅንጅት ሰርተዋል። በሀገርም ላይ ክህደት ፈጽመዋል። ኢትጵያውያንም ይቅር የማይሉት በደልም አድርሰዋል።

በቅርቡ የብሄራዊ ደህንነት ምክር ቤት ይፋ እንዳደረገውም የጸጥታ ኃይሉ በወሰደው እርምጃ የሸኔ እና ሕወሓት የሽብር ቡድኖችና የሌሎች አገር ዜጎች ከአልሸባብ ጋር በጋራ ተሰልፈው ተገኝተው ተደምስሰዋል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ የውስጥና የውጭ ጠላቶች ተቀናጅተው ኢትጵያን ለማፍረስ ሌት ተቀን እየሰሩ መሆኑን የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች አሉ። የህን መሰል የጥፋ ዕቅድ በኢትጵያ ላይ ቢታቀድም ምስጋና ለተቀናጀው የጸጥታ ኃይላችን ይሁንና በትልቅ መስዋዕትነት የኢትዮጵያ ጠላቶች የከፋት ሴራ ሊከሽፍ ችሏል። ይህም ትልቅ ከብር የሚያሻው አኩሪ ተጋድሎ መሆኑን መመስከር ይቻላል። የጸጥታ ኃይሉ ከሚያደርገው ሀገርን የማዳን ጥረት በሻገር የኢትዮጵያን መቀጠል የሚሻ ማንኛውም ዜጋ የሀገሩን ሰላምና ጸጥታ ማስጠበቅ ዋነኛ ስራ አድርጎ ሊይዝ ይገባል።

የውስጥና የውጭ ጠላቶች ዋነኛ ዓላማ ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር ማፍረስና ከካርታ ላይ መፋቅ ነውና ይህ እኩይ ዓላማቸው እንዳይሳካ ከጸጥታ ኃይሎች ተጋድሎ ጎን ለጎን ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሀገራቸውን በማዳኑ ተግባር ላይ ፊና ወጊ ሆነው መገኘት አለባቸው። ለዚህም ሲባል ጥቃቅን ልዩነቶችን ወደ ጎን በመተው የጠላቶችን እኩይ ሴራ መበጣጠስና በተለይም በዚህ ወቅት ሀገርን መታደግ ይገባል።

የጸጥታ ኃይሉ የሚያካሂደውን ሀገርን የመታደግ ተልዕኮ በማገዝና ዋነኛ ተዋናይም በመሆን የማትተካውን ሀገር ከጥፋት መታደግ የዚህ ዘመን ትውልድ ዋነኛ ተልዕኮ መሆኑም መዘንጋት የለበትም። በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ የጸጥታ ኃይሉና ሕዝቡ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ፣ እንደ አንድ ልብ መካሪ በመሆን ኢትዮጵያን ልትደርስ ካሰበችበት የብልጽግና ማማ ላይ ማድረስ ተገቢ ነው!

ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - - 011-156-98-73

ፋክስ 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

# ሕዝቡን ከምሬት ወደ እፎይታ የማሻገር የቤት ሥራ

**በየኔነው ስሻው**

ሰላም፣ ልማት እንዲሁም ዴሞክራሲ በአንድ አገር ውስጥ አስፈላጊ የመሆናቸው ጉዳይ የሚያጠያይቅ ባይሆንም፤ አንዳቸው በአንዳቸው ውስጥ የሚገለጡ፣ አንዳቸው ለሌላቸው መሰረት እንደሆኑም የሚናገሩ በርካቶች ናቸው። ያለ ሰላም ልማት፤ ያለ ልማትና ሰላም ደግሞ ዴሞክራሲ የማይታሰብ፤ ሊሆንም የማይችል ነው ሲሉም ይሞግታሉ። ምክንያቱም በአንድ አገር ውስጥ ሰላም በሌለበት ልማትና ብልጽግናን እውን ማድረግ አይቻልም፤ ልማትን እውን ማድረግ ቀርቶ የለማውን ኢኮኖሚ እንኳን ባለበት ማስቀጠል እጅጉን ፈታኝ ነው። ምክንያቱም ኹከት፣ ግርግርና ግጭት ባለበት አገር ውስጥ ሀብትን ለልማት ሳይሆን ለጦርነትና መልሶ ግንባታ ማዋል ላይ ትኩረት መደረጉ፤ በተቃራኒው የለሙ መሰረተ ልማቶች ለውድመት መጋለጣቸው ደግሞ እንደማሳያ ይጠቅሳሉ።

እንደ ልማት ሁሉ ዴሞክራሲን እውን ለማድረግ ሰላም እጅጉን ወሳኝ መሆኑም ነው የሚነገረው። የሰላም መደፍረስ ባለበት፣ ጦርነትና አለመረጋጋት እንዲሁም የደህንነት ስጋት በሚስተዋልበት አገር ውስጥ ስለ ዴሞክራሲ ማሰብ የቅንጦት ያህል መሆኑን የዘርፉ ሰዎች ያስረዳሉ። ሰላምን ለማስፈን እንዲሁም የአገር እና የሕዝብን ህልውና ለማስጠበቅ ሲባል የሚጣሉ ገደቦች፤ የሚወሰዱ እርምጃዎች በዜጎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ላይ የሚፈጥሩት ጫና መኖሩን እንደ አብነት ይጠቅሳሉ። እንደ ሰላም ሁሉ በልቶ የማደር ሕልውናውን ባላረጋገጠ አገር ውስጥ ስለ ዴሞክራሲ ማሰቡ ባዶ ተስፋ መሆኑ የታወቀ ነው። በመሆኑም በአንድ አገር ልማትን እውን ለማድረግ፣ ዴሞክራሲንም ለማረጋገጥ ሰላም ወሳኝና መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን አበክረው ይገልጻሉ።

ስለ ሰላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ቁርኝት ይሄን ያህል ካልኩ፤ እነዚህ ሶስት ነገሮች በአንድ አገር እንዲኖሩም ሆነ እንዳይኖሩ በማድረግ ሕዝብ ለምሬት አልያም እፎይ ብሎ በተረጋጋ መንፈስ እንዲኳዝ የሚያደርጉ ገፊ ምክንያቶች አሏቸው። እነዚህ ገፊ ምክንያቶችም ተወራራሽነት ያላቸው፤ አንዱ ምክንያት ለሌላው መነሻ የሚሆኑ ናቸው። ለምሳሌ፣ የኮንትሮ ባንድ ንግድና ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር በአንድ በኩል በኢኮኖሚ ላይ የሚሰራ ሻጥር ሲሆን፤ በሌላው ጎኑ ደግሞ የሰላም መደፍረስ ሁነኛ መነሻ ነው። በተመሳሳይ ይሄን የሰላምና የኢኮኖሚ በሽታ ለማስወገድ በሚወሰድ እርምጃ በሰዎች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ላይ የሚጥለው ገደብ ይኖራል።

በዚህ መልኩ የሚገለጹ በርካታ ምክንያቶች ያሉ ቢሆንም፤ ዛሬ ላይ በኢትዮጵያ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ሕዝቡን ለምሬት የዳረጉና ጎልተው የሚታዩ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች አሉ። እነዚህም ሕዝቡ ወጥቶ የመግባት ስጋት ውስጥ እንዲገባ፤ በልቶ የማደር ሕልውናው እንዲፈተን፤ ማሕበራዊ ቁርኝቱ እንዲላላና እርስ በእርሱ እንዲገፋፋ እያደረጉት ያሉ ሲሆን፤ እነዚህን ችግሮች ላይቶ መፍትሄ መስጠት ደግሞ ለነገ የማይባል ይልቁንም ሕዝቡ ከችግሮቹ ባሻገር ያሉ የልማትና ብልጽግና መዳረሻዎቹን እንዲመለከት ማስቻል ነው። ከሰሞኑም ብሔራዊ የደሕንነት ምክር ቤት ባካሄደው ግምገማም ይሄንኑ የለየ ሲሆን፤ ሕዝቡን በሚያማርሩ የኢኮኖሚ አሻጥር፣ የሙስና፣ የኮንትሮባንድ፣ ሕገወጥ የገንዘብ ዝውውር ወዘተ ላይ የማያዳግም እርምጃ በመውሰድ ሕዝቡ እፎይ እንዲል ማድረግ እጅጉን አስፈላጊ እና ለዚሁ ሁሉም የራሱን የቤት ስራ ሊወጣ እንደሚገባም ነው ያሳሰበው።

ይህ ግምገማና አቅጣጫ ዛሬ ላይ ሕብረተሰቡ ላለበት ችግር መፍትሄ ያገኘ ዘንድ አንድ እርምጃ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። ምክንያቱም ሕዝቡ ዛሬ ላይ የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት እጅጉን ምሬት ውስጥ የከተተው፤ ውሎ ካደረም የሰላም ስጋት ወደሚሆንበት ደረጃ የሚያመራው ስለመሆኑ ሕዝቡን ቀርቦ ማየትና ሕዝቡ ውስጥ መኖር ብቻ በቂ ነው። በተመሳሳይ ሰላምና ደህንነቱ በከተማውም ሆነ በገጠሩ ማሕበረሰብ ላይ የስጋት ጥላውን ከማጥላቱም በላይ፤ የችግሩ ገፈት ቀማሽ አድርጎታል። ከሞተው ንብረቱን በጠራራ ፀሐይ እየተቀማ፣ አካላዊ ደሕንነቱም ሆነ የሕይወት ደሕንነቱ በአንድ ዘራፊ ወንበዴ በድንገት የሚወሰንበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በገጠሩ አካባቢም ቢሆን ሕብረተሰቡ ለሕይወቱም፣ ለንብረቱም ከለላ የሚሆነው አጥብቆ የሚሻበት፤ በሽብርተኞች መዳፍ ውስጥ ሲወድቅም በደቂቃ ውስጥ ሕይወቱንም፣ ንብረቱንም የሚነጠቅበት፤ ለከፋ አካልና ሥነልቡና ጉዳት፣ መፈናቀልና ስደት የሚዳረግበት ወቅት ነው።

በተመሳሳይ፣ ሕወገ ወጥ የገንዘብ ዝውውር፣ የኮትሮባንድ ንግድ፣ የኢኮኖሚ አሻጥርና ሙስና ሌላው የማህበረሰቡ ትብታብ ሆነው አላላውስ ያሉት፤ ለሰላሙም ሆነ በልቶ ለማደሩ ስጋት ላይ እንዲወድቅ ከፍተኛ ሚና እየተጫወቱ ያሉ ከፉ ተግባሮች ናቸው። እነዚህ ከአገር በላይ ስለ ግል ጥቅምና ከፍታ ሲባል የሚፈጸሙ ፀረ ሕዝብና አገር ተግባራት፤ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያን ለከፋ የሰላም እና የኢኮኖሚ ስብራት፤ ኢትዮጵያውያንንም ከፍ ላለ የሰላምና ደሕንነት እንዲሁም የኑሮ ውድነት ችግር ዳርገው ሕልውናቸውን እየተፈታተኑ ይገኛሉ። በእነዚህ ከፉ ተግባራት ምክንያት ሕዝቡም ስለ ነገ ልማትና ብልጽግናው ሳይሆን ስለ ዛሬ ሕልውናው ብቻ እንዲጨነቅ፤ እፎይታ አልባ የምሬት ኑሮን እንዲገፋ ሆኗል።

ይህ ምሬትና የሕልውና ስጋት ደግሞ ውሎ ሲያድር የራሱ የሆነ አደጋን መጋበዙ፤ የላቀ ስጋት መሆኑ አይቀሬ ነው። ብሔራዊ የደኅንነት ምክር ቤቱም ችግሩን ገምግሞ አቅጣጫ ሲያስቀምጥ ይሄንኑ በመረዳት ነው። ከዚህ አኳያ ችግሩን ከማቃለል አኳያም የተጀማመሩ ተግባራት መኖራቸው እሙን ነው። ይሁን እንጂ፣ የችግሩን ስፋትና ግዝፈት የመጠነ ስልት ነድፎ መስራት፤ በሂደቱ የሚታዩ እንከኖችን ያለ አንዳች ማመንታት እየነቀሱ ማውጣትና እርምጃ መውሰድ፤ ለዚህ ደግሞ ሁሉም ኃላፊነቱን የሚወጣበትንና ባይወጣ ሊደርስበት የሚችለውን የተጠያቂነት ልክ አስገንዝቦ በሙሉ ልብና አቅም መስራትን ይጠይቃሉ።

ትልቁ የቤት ስራም የሚሆነው ይሄው በሙሉ ልብና አቅም ችግሮችን እፈታለሁ፤ የሕዝቡን ምሬት በእፎይታ ለመተካት አስፈላጊውን መስዋዕትነት እከፍላለሁ ብሎ ወደ ተግባራዊ እርምጃ መግባቱ ነው። ምክንያቱም ስራው ከቃል ያለፈ ተግባርን፤ ከማስመሰል የተሻገረ ራስን አሳልፎ መስጠትን፤ ከመሸንገል የላቀ የሕዝብ ወገንተኝነትና ተቆርቋሪነትን፤... የተላበሰ አመራር፣ ባለሙያ፣ እንዲሁም ሕዝብ በእጅጉ ይፈልጋል። ይሄን ሆኖ መገኘት ደግሞ ከሁሉም የሚጠበቅ፤ ከራስ በላይ ስለ አገርና ሕዝብ አለኝታነትን የመግለጥ እውነት ነው። እናም ሕዝብ ከምሬትና የሕልውና ስጋት የሚላቀቅበት ጊዜ እንዳይርቅ ሁሉም በያለበት ቦታና መስክ ሁሉ በኃላፊነቱ ልክ የቤት ስራውን ወስዶ ሊወጣ ይገባል።

# ፍረዱኝ

# ‹‹ፍርድ ተዛብቶብኛል ፤ ሰበር ቅስሜን ሰብሮኛል››

## አቤቱታ አቅራቢ አቶ ዘመረ ጀማነህ

ክፍለዮሐንስ አንበርብር

**ጉዳዩ**

አቶ ዘመረ ጀማነህ ይባላሉ። የ80 ዓመት አዛውንት ሲሆኑ በፍርድ ሂደት ውስጥ የተዛባ ውሳኔ ተላልፎብኝ በስተእርጅና ስለ ፍትህ እያልኩኝ ነው ይላሉ። ነዋሪነታቸውም ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ቤት ቁጥር 405 የራሳቸው መኖሪያ ቪላ ነበር። 1965 ዓ.ም ጀምሮ አብሯቸው ጋብቻ የፈፀሙት ባለቤታቸው ወይዘሮ አልማዝ አስፋው እና አራተኛ ልጃቸው ዳዊት ዘመረ በዚህ ቤት ውስጥ ነበሩ። ዳሩ ግን በሂደት የህይወት ምህዋሯ ተቀይሮ ሰለማዊ የነበረው ህይወት ተናጋ፤ አምቧጓሮ ተበራከተ።

አቶ ዘመረ እንደሚሉት፤ ያልጠበቁት የቤተሰብ ግጭት በመፈጠሩ ከቤት ለመውጣት ተገደዋል። በተለይም ደግሞ ለዚህ ሁሉ ግጭት ትልቁን ሚና ይወስዳል የሚሉት የገዛ አብራካቸውን ክፋይ ልጃቸውን ነው። በዚህም የተነሳ እርሳቸው ሻንጣቸውን ሸክፈው 1997 ዓ.ም ከቤት ወጡ። በዚህ ሁኔታ አብሮ መቀጠል ለህይወቴም ስጋት የፈጠረብኝ ስለነበር ነው ቤቱን ጥዬ የወጣሁት ይላሉ።

አቶ ዘመረ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 02 ቤት ቁጥር 405 ከባለቤታቸው ጋር ከነበሩበት ቤት ወጥተው ወደ ላፍቶ ክፍለ ከተማ ጎተራ አካባቢ ካራሶሪያ አስመራ የሚባለው ፖሊስ መምሪያው አካባቢ ሌላ ቤት መኖር ጀመሩ። ምንም እንኳን ከባለቤታቸው ቢርቁም 1997 ዓ.ም እስከ 2000 ዓ.ም ድረስም የቤት ወጪ እየሸፈኑ የብቸኝነት ኑሯቸውን ቀጠሉ። ነገር ግን ከመከሰስ አልዳኑም።

**ልደታ ችሎትና ፍቺ**

ባለቤታቸው ወይዘሮ አልማዝ አስፋው እና የአብራካቸው ክፋይ የሆነው የጋራ ልጃቸው ዳዊት ዘመረ በጋራ ሆነው የፍቺ ጥያቄ ለልደታ ክፍለ ከተማ ማቅረባቸውን ይናገራሉ። በዚህም 1965 ዓ.ም የተፈፀመው አቶ ዘመረ ጀማነህ እና ወይዘሮ አልማዝ አስፋው ጋብቻ ሐምሌ 1ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ እንዲፈርስ ተወሰነ። በልደታ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት የ1965 ዓ.ም ጋብቻ መፍረስ ከውሳኔ ደረሰ። በዚሁ ክርክሩ ቀጥሎ በ2002 ዓ.ም ከፊል የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ተደረገ። በፍርድ አፈፃፀሙም 24 ቀን ቆጠራ ተካሂዶ የከባድ ተሽከርካሪዎች መለዋወጫ ክፍፍል ተደረገ። አቶ ዘመረ ቀደም ሲል የከባድ ተሽከርካሪዎች መለዋወጫዎችን ይነግዱም ነበር። ታዲያ በክፍፍሉ ወቅት የትዳር አጋራቸው የነበሩት ወይዘሮ አልማዝ የሚገባቸውን ድርሻቸውን ወስደው ቦሌ ክፍለ ከተማ ወደ ነበረ ቤታቸው አመሩ፤ በዚያው መኖርም ጀመሩ።

በ2003 ዓ.ም ደግሞ የመጨረሻው የንብረት ክፍፍል ውሳኔ ተሰጠ። በዚህም የሦስተኛ ወገን ንብረት ነው ተብሎ የነበረው ጉዳይ ላይ ወይዘሮ አልማዝ ቅር ተሰኝተው ስለነበር ወደ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቅሬታ አቀረቡ። የሦስተኛ ወገን ንብረት ተብሎ የነበሩት ካዛንቺዝ አካባቢ የነበረ መሬትና ቤት ነበር። ይሁንና ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ሲያጣራ ከቆየ በኋላ ንብረቱ የሚመለከተው ካርታውም ሆነ ግዥው የተካሄደው በጋራ ሴት ልጃቸው መሆኑ ተረጋገጠ። ንብረቱም ሁለቱንም የማይመለከትና የሦስተኛ ወገን መሆኑን ተረጋገጠ። በዚህም ላይ የነበረው ክርክር መቋጫውን አገኘ።

አሁንም የትዳር አጋራቸው የነበሩት ወይዘሮ አልማዝ ቅሬታቸውን ይዘው ወደ ልደታ ምድብ ችሎት ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤት አሉ። እስከ 2004 ዓ.ም ክርክሩ ቀጠለ። በዚህ መሃል ግን የአራት የቤተሰብ አባላትን ግጭት በውል የተረዱ አካላት ይህን በሠላማዊ መንገድ ብትፈቱስ ብለው መከሯቸው። አቶ ዘመረም ከቤተሰብ በላይ ምን አለ፤ እርቅንስ ማን ይጠላል ሲሉ እሽታቸውን ገለፁ። በዚህም ጊዜ ሽማግሌዎች ተመርጠው ወደ እርቅ መንገድ ለመሄድ ከሥምምነት ተደረሰ።

**የእርቅ ሥምምነት**

ይህ ቤተሰብ መበተን የለበትም የሚሉ አካላት ወደ እርቅ እንዲያመሩ የሚጠበቅባቸውን ሥራ ጀመሩ። የዕርቅ ስምምነት መግቢያውም እንዲህ ይላል። የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት 1ኛ ፍትሃብሄር ችሎት በአንድ በኩል በወይዘሮ አልማዝ አስፋው እና በአቶ ዘመረ ጀማነህ እንዲሁም በጣልቃ ገብ ወይዘሮ ዕፀሕይወት ዘመረ መካከል ያለው የቤተሰብ ጉዳይ በሌላ በኩል በአቶ ዘመረ ጀማነህ እና በአቶ ዳዊት ዘመረ መካከል ያለው የፍትሀብሔር ክርክር በአስታራቂ የሽምጋዮች ጉባኤ ዓማካኝነት በዕርቅ እንዲጠናቀቅ ባዘዘው መሠረት ጉባኤው ባደረገው ከፍተኛ ጥረት የፈጣሪም ኃይል ተጨምሮበት ቤተሰቡ ጉዳያቸውን በዕርቅ ጨርሰው ልዩነታቸውን ሙሉ በሙሉ በማስወገድ እንደሚከተለው የዕርቅ ስምምነታቸውን አድርገዋል።


አንደኛ ወይዘሮ አልማዝ አስፋው እና አቶ ዘመረ ጀማነህ ቀደም ሲል የነበራቸው ትዳር (ጋብቻ) በፍርድ ቤት የፍቺ ውሣኔ ፈርሶ የነበረ በመሆኑ እንደገና በአዲስ መልክ ሕጋዊ ጋብቻ በማድረግ በሰላም አብረው ለመኖር በሙሉ ፈቃደኝነት ስምምነት አድርገዋል። ሆኖም የቀድሞው ትዳር በፍርድ ቤት የፍቺ ውሣኔ ከፈረሰ በኋላ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት እና ሀብት ክፍፍል አስመልክቶ የመጨረሻ የፍርድ ቤት ውሣኔ በማግኘት ክፍፍል ያልተደረገ በመሆኑ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ልደታ ምድብ 4ኛ ፍትሃብሔር ችሎት በኮድ መለያ ቁጥር 142607 በ28/11/03 በዋለው ችሎት የባልና ሚስት የጋራ ሀብትን አስመልክቶ በሰጠው ፍርድ የተጋቢዎቹ የጋራ ሀብት ናቸው ያላቸውን ንብረቶች በአንድ ላይ በማጣመር አዲስ ጋብቻ በመፈፀም አብረው ለመኖር ስምምነት ላይ ደርሰዋል። የ3ኛ ወገኖች ንብረትን አስመልክቶ ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ ሁለቱም ወገኖች በዚህ የዕርቅ ስምምነት በሙሉ ፈቃደኝነት መቀበላቸውን አረጋግጠዋል።

በመሆኑም የጋራ ንብረት ክፍፍልን አስመልክቶ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 115327 ያለው የይግባኝ ክርክር በዚህ የዕርቅ ስምምነት መሠረት እንዲዘጋ ስምምት ላይ ተደርሷል።

ሁለተኛ በአቶ ዘመረ ጀማነህ እና በአቶ ዳዊት ዘመረ መካከል ያሉት የፍትሃብሔር ክርክሮች አቶ ዳዊት ዘመረ በወላጅ አባቱ ላይ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ላደረሰባቸው ጉዳት በማልቀስና እግራቸው ላይ ወድቆ ይቅርታ በመጠየቁ ወላጅ አባቱ ይቅርታውን ተቀብለዋል። አቶ ዘመረ ጀማነህ እና ወይዘሮ አልማዝ አስፋው ልጃቸው አቶ ዳዊት ዘመረ ከእስር በሚፈታበት ወቅት ራሱን ችሎ ከወላጆቹ ተለይቶ እንዲኖር ተስማምተዋል። አቶ ዳዊት ዘመረም እራሱን ችሎ እንዲኖር ያስችለው ዘንድ በሱ ሥም ተመዝግቦ የሚታወቀው 548ሺ.500 ብር የሚያወጣ የአዋሽ ኢንሹራንስ ኢንሹራንስ እና ከሼሩ የተገኘ ዲቪደንድ ከ250ሺ. ብር በላይ ክፍያ የተጠራቀመለት ገንዘብ በበቂ ሁኔታ ሊያቋቁመው እንደሚችል ተስማምተዋል።

በተጨማሪ አቶ ዘመረ ጀማነህ በአቶ ዳዊት ዘመረ ላይ የመሠረትዋቸው በመ/ቁ 01595 እና በመለያ ቁጥር 71986 የፍትሃብሔር ክርክሮች በዚህ የዕርቅ ስምምነት በራሳቸው ተነሳሽነት እንደሚያቋርጡ ፈቃደኛነታቸውን አረጋግጠዋል። አቶ ዳዊት ዘመረም ከቤተሰቡ እራሱን ለማስቻል የተደረገለትን ስጦታ በመቀበል የራሱን ሕይወት ከወላጆቹ ቤት በመውጣት እንደሚመራ ስምምነቱን በዚህ የዕርቅ ስምምነት አረጋግጧል።

ሦስተኛው ሁሉም የቤተሰብ አባላት ባሉበት ከልብ የመነጨ ይቅር ባይነት ባለበት ሁናቴ በሙሉ ፈቃደኝነት እና ቅንነት ይህ የዕርቅ ስምምነት የተደረገ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ ያሉትም የቤተሰቡ አባላት በሚገኙበት አንድ የጋራ ጉባኤ የቤተሰቡን ሕይወት ወደነበረበት የሚመልስ አንድ አጋጣሚ ለመፍጠር ጉባኤው እና ታራቂዎቹ ተስማምተዋል ይልና አምስት አስታራቂዎችና አራት ታራቂዎች ፊርማ ያለበት ሰነድ ያስረዳል። በዚህ የእርቅ ሥምምነት በርካታ የንብረትና እና ቤተሰባዊ ጉዳዮች የተገለፁ ቢሆንም ለእርቁ ስኬታማ መሆንና ቀጣይ መሆን በቅድመ ሁኔታ የተቀመጡ ነበሩ።



ፎቶ:- አዩብ ተፈሪ

**ያልተፈፀመው ቅድመ ሁኔታ**

ከሁሉም በላይ ግን ለዕርቁ ተፈፃሚነት የሚከተሉት ነጥቦች በግልጽ ተቀምጠው ነበር ይላሉ አቶ ዘመረ። እነዚህም ቀደም ሲል ክፍፍል ተደርጎበት የነበረው ንብረት ወደቦታው ተመልሶ የጋራ እንዲሆን፤ የሦስተኛ ወገን ተብሎ የተወሰነ ዳግም ተመልሶ ጥያቄ እንዳይነሳበትና የሌላ አካል ንብረት ስለመሆኑ፤ የ1965 ዓ.ም ጋብቻ በፍርድ ውሳኔ የፈረሰ በመሆኑ በድጋሚ ጋብቻ ለማድረግ፣ አቶ ዳዊት ዘመረ እድሜው ከ40 ዓመት በላይ ስለሆነ እና ባሕሪው ለጋብቻው ዳግም መከናወን ሆነ ሌሎች የባልና ሚስት ሁለትዮሽ ጉዳዮች አስቸጋሪ በመሆኑ ተመልሶ ወደ ወላጆች እንዳይመለስ፣ እንደ አዲስ ለሚመሰረተው ጋብቻ እንቅፋት ስለሚሆን ሁኔታዎች እንዲመቻቹ የሚሉ ናቸው።

ዳዊትም የራሱን ሕይወት ይመራበት ዘንድ 550ሺ ብር የሚያወጣ ከአዋሽ ኢንሹራንስ አክሲዮን መርቀው መስጠታቸውን ይናገራሉ። እንዲሁም 250ሺ ዲቪደንድም ስለነበረው ይህን እያንቀሳቀሰ መኖር ይችላል የሚል ነው። ይሁንና እነዚህ ጉዳዮች በሙሉ ተፈፃሚ ባለመሆናቸው አቶ ዘመረ ከባለቤታቸው ጋር መቀጠል አልቻሉም። በዚህም የተነሳ ቅድመ ሁኔታዎቹ ዋጋ ቢስ ሆነዋል ይላሉ።

ታዲያ ይህ ቅድመ ሁኔታ ባለመሟላቱ በ2003 ዓ.ም ቀደም ሲል በተሰጠው የፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት ንብረት ክፍፍል ለማድረግ ተስማሙ። ለዚህም ዳግም ወደ ልደታ መጀመሪያ ደረጃ ቤተሰብ ችሎት አመሩ። ችሎቱም በንብረት ላይ እግድ ጥለው ለነበሩ ድርጅቶች ትዕዛዝ እንዲሰጥና እንዲከፋፈል ደብዳቤ ፃፈ። በዚህ መሰረትም ወይዘሮ አልማዝና አቶ ዘመረ በጋራ ፊርማ ለእያንዳንዱ ተቋማት ደብዳቤ ፃፉ። የሁለቱን አመልካቾችን ሃሳብና ፍላጎት መሰረት በማድረግም የንብረት ክፍፍሉን በዓደባባይ አከናወኑ። ይህን ያደረጉ ድርጅቶችም በፊርማ እና ማህተም አረጋግጠው ለሁለቱም ወገኖች ማስረጃ ሰጥተዋል። ይህንንም ማስረጃም ለፍርድ ቤት አቅርበዋል-አቶ ዘመረ ጀማነህ። ቦሌ ክፍለ ከተማ ከሚገኘው ቤት በስተቀር ሁሉም ክፍፍል ተደረገ።

በክፍፍሉም መሰረት ወይዘሮ አልማዝ አስፋው ኮድ2-08823 ቮልስዋገን እና ኒሳን የጭነት መኪና የሆነና ሰሌዳ ቁጥሩ 2-12568 ወስደዋል። ዳሩ ግን አቶ ዘመረ የቦሌውን ቪላ ቤት ሊካፈሉ አልፈለጉም። ምክንያቱ ደግሞ የልጆቼ እናት ማረፊያ የት ይሆናል የሚለውን የሞራል ጥያቄ ከግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑም ይናገራሉ። ሚያዚያ 28 ቀን 2004 ዓ.ም የተፈፀመው ዕርቅ ሥምምነት ገቢራዊ ባለመሆኑም ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ግንቦት 2 ቀን 2004 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጠ። ትዕዛዙም በእርቁ ስምምነት መሰረት ይፈፀም የሚል ነበር። በዚህም ሃምሌ 2004 ዓ.ም ክፍፍል ተጀመረ። በዚህ ወቅትም በሁለቱም ጎን ንብረት ቆጠራ ተካሂዶ ክፍፍሉ ተጠናቀቀ። በዚህ ወቅትም ያረካከቡ ምስክሮች ነበሩ። ከፊል ክፍፍል ቀርቶ ወደ ሙሉ ክፍፍል አመራ።

**ክስ እንደገና**

አቶ ዘመረ እንደሚሉት፤ 1965 ዓ.ም ጋብቻ በ2001 ዓ.ም ፈርሶ፤ ንብረት ክፍፍሉ ደግሞ በ2004 ፍፃሜውን አገኘ። ሁለታችንም የራሳችን ሕይወት ጀመርን። ሆኖም ከ10 ዓመታት ቆይታ በኋላ አቶ ዘመረ እንደገና በወይዘሮ አልማዝ አስፋው ክስ ቀረበባቸውና ችሎት ፊት ቀረቡ። በዚህም ቦሌ የመጀመሪ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት ቀርበው ክሱን አዳመጡት።

የክሱ ጭብጥም በ2004 ዓ.ም የተፈራረምነው የዕርቅ ሥምምነት ትዳራችንን ወደነበረበት መልሶታል። በመሆኑም አልተለያየንም፤ ንብረትም አልተከፋፈልንም፤ አብረንም ንብረት አፍርተናል የሚል ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት ግን አብረን መኖር ባለመቻላችን የ1965 ዓ.ም ጋብቻ ይፍረስ የሚል ነበር።

# ፍረዱኝ

ዳሩ ግን ይላሉ አቶ ዘመረ፤ ጋብቻችን ፈርሶ ንብረትም ተከፋፍለን ነበር። በዚህ አካሄድ የፈረሰው ጋብቻ እንዲፈርስ የሚል ነው። በዚህም የተነሳ እንዲህ ብለው ለችሎቱ አስረዱ። 1965 ዓ.ም የተፈፀመው ጋብቻ ቀደም ሲል በ2001 ዓ.ም መፍረሱንና ንብረት ስለመከፋፈላቸውም 17 መረጃዎችን አቀረቡ። እነዚህ መረጃዎችም ምስክሮች ቆመው ያከፋፈሉትና የተረካከቡበትና የተፈራረሙትን ሰነድ፤ የባንክ ቤት የክፍፍል ሰነዶችና የመሳሰሉትን ያካትታል። ይህም ብቻ ሳይሆን ሁለቱም ያላገባ ሰርተፍኬት ማውጣታቸውን አስረዱ። ባለቤታቸው የነበሩት ወይዘሮ አልማዝም ቀደም ብለው ከኩነት ምዝገባ ጽህፈት ቤት ያላገባ ሰርተፍኬት ስለማውጣታቸውም ፍርድ ቤት ጭምር ቃላቸውን ሰጥተዋል፤ በሰነድም የተደገፈ ሆኖ ተገኘ።

በእነዚህ ዓመታት ውስጥ ንብረት ሸጠዋል፤ ለውጠዋል። በእነዚህ አስር ዓመታት ውስጥ አቶ ዘመረ በርካታ የግል ንብረት ማፍራታቸውንና በሌላ የህይወት መስመር እየተጓዙ እንደነበርም ይናገራሉ። ወይዘሮ አልማዝም በክፍፍሉ የደረሳቸውን የአዋሽ ባንክ አክሲዮን ሸጠው ዕዳ መክፈያ ስለማድረጋቸውም ዋቢ አድርገው ለችሎቱ አቀርበው ነበር። ይህም ብቻ ሳይሆን ከንብ ባንክም አክሲዮን እያንዳንዳቸውም አንድ ሚሊዮን ስለመከፋፈላቸውም አስገነዘቡ። ከንብ ኢንሹራንስም የሚገባቸውን መከፋፈላቸውን አስረዱ። ይህ በቃል የሆነ ነገር ሳይሆን በሰነድ የተደገፈ ሆኖ ተገኘ።

በዚህ የክርክር ሂደት የቦሌ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም፤ የ1965 ዓ.ም ጋብቻ ስለመፍረሱ እና የእርቅ ስምምነቱ ወደነበረበት እንደማይመልሰው አረጋገጠ። ሆኖም እርቅ ሥምምነት ሲፈረም አዲስ ጋብቻ እንደተፈፀመ ይቆጠራል ይልና፤ ስለዚህ 2004 ዓ.ም ህጋዊ ጋብቻ ከዛሬ ጀምሮ እንዲፈርስ ወስኛለሁ ሲል የ2004 ዓ.ም የተከናወነውን እርቅ ጋብቻ እያለ በመጥራት ብያኔ ሰጠ።

በዚህ ጊዜ አቶ ዘመረ ለቦሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አሉ። የይግባኙ ፍሬ ነገርም ፍርድ ቤቱ ያልተጠየቀ ጥያቄ ላይ ምላሽ መስጠቱ አግባብ አይደለም የሚል ነው። እየተጠየቀ ያለው በ2001 ዓ.ም ስለፈረሰ ጋብቻ እና በይፋ ስለተከናወነ፤ በሰነድ ስለተደገፈ ንብረት ክፍፍል ሆኖ እያለ 2004 ዓ.ም የተደረገን የእርቅ ስምምነት እንደ ጋብቻ መቁጠሩ አግባብ አይደለም የሚል ነው።

ዳሩ ግን ወይዘሮ አልማዝም የቦሌ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተመሳሳይ ይግባኝ አሉ። እነርሱ ደግሞ ያልጠየቅነውን ጉዳይ ተፈረደልን የሚል ነበር። ጥያቄያችን 2004 ዓ.ም ጋብቻ ሳይሆን 1965 ዓ.ም ጋብቻ ይፍረስ ብለን ነው ሲሉ ነበር ይግባኝ ያሉት። ጉዳዩ ግን በዚህ ችሎት አላበቃም። ወደ ሌላ የክርክር ሂደት ተሸጋገረ።

**ወደጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የሁለቱ ክርክር አልበቃ በማለቱ እየተራዘመ በመሄዱ ወደ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደረሰ። ጠቅላይ ፍርድ ቤት በበኩሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወሰነውን ሽሮ እና የሥር ፍርድ ቤትን ፍርድ አሻሽሎ 1965 ዓ.ም ጋብቻ ይፍረስ ሲል ወሰነ።

ጠቅላይ ፍርድ ቤት፤ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጋብቻ ስላልተመሰረተ ብሎ የፈረደው ፍርድ ትክክል አይደለም። ምክንያቱም ደግሞ በሰበር ውሳኔ መዝገብ ቁጥር 23021 መሰረት ሁለት ባልና ሚስት ከተፋቱ በኋላ አብረው እንደባልና ሚስት ከሆኑ እንደ ጋብቻ ይቆጠራል ብሎ የወሰነው አመክንዮ አድርጎ አቀረበ።

ይሁንና ይላሉ አቶ ዘመረ መዝገብ ቁጥር ‹‹23021›› ከእኔ ጉዳይ ጋር አንዳችም አይገናኝም። የተጣመመ ትርጉምና ሂደት ነው። በዚህ መዝገብ የተወሰነው ውሳኔ ንብረት ባልተከፋፈሉ ሁለት ግለሰቦች መካከል ስለላው ጉዳይ የሚያወራ እንጂ ለዚያውም ደግሞ ለአራት ወራት ስለተለያዩ ግለሰቦች እንጂ የእኔን ጉዳይ የሚዳስስ አይደለም ሲሉም ያስረዳሉ። ‹‹እኔ ጋብቻችን ስለመፍረሱ ማስረጃ ያለኝ፤ ንብረት በገሃድ የተከፋፈልኩ፣ ሁለታችንም ያላገባ ሰርተፍኬት ያወጣን›› ሆኖ ሳለ የማይገናኝ የውሳኔ መዝገብ መጠራቱ ፍርድ ስለመጣመሙ ሁነኛ ማስረጃ ነው ሲሉ ይሞግታሉ። ታዲያ በዚህ ሂደትና ፍርድ አመኔታ ያጡት አቶ ዘመረ ጀማነህ ወደ ሰበር ችሎት ለማምራት ወሰኑ።

**የሰበር ችሎት**

የክርክር ሂደቱ ከሥር ፍርድ ቤት ጀምሮ ጠቅላይ ፍርድ ቤትንም አልፎ ወደ ሰበር ችሎት ደረሰ። አቶ ዘመረም ሰበር አጣሪ ችሎት ያቀረቡት ቅሬታና አቤቱታ ወደ ሰበር የሚያስኬድ ነው በማለት ሦስት ዳኞች ጉዳዩን መርምረው ወደሚመለከተው አካል አሳለፉት። በዚህ ክርክር ሂደት የፍትሃብሔር ህግ ከ1731 እስከ 1733 በጋብቻ ውል መሰረት ታይቶ መፈረድ አለመፈረዱ ይታይ የሚለውንም መርምሯል። በዚህ የክርክር ሂደት የአቶ ዘመረ ጉዳይ ሰበር መቅረቡ ግድ ሆነ።


በሰበር ችሎት አምስት ዳኞች ተሰይመው ጉዳዩን ግራ ቀኝ መርምረናል ሲሉ አሳወቁ። ፍርዱን አፅንተናል ሲሉም ደመደሙ ይላሉ። በዚህም የሰበር ውሳኔ ከታች ጀምረው የተበላሹ ውሳኔዎች ጠልቀው ምርምር ሳይደረግባቸው ተወሰነ ይላሉ። ተስፋ ያደረኩበት ሰበር ቅስሜን ሰብሮኛል፤ አግባብም ያልሆነ ፍርድ ፈርዶብኛል ሲሉ ለኢትዮጵያ ህዝብ ይፈረደኝ ሲሉ አቤት ይላሉ።

አቶ ዘመረ እንደሚሉት፤ ህግ ስለመጣሱ ባመለከትም፤ ፍርድ ስለመጣመሙም ማስረጃ ጭምር ባቀርብም ምንም ሰሚ ማጣቴ ያሳዝናል ባይ ናቸው። በሁሉም ክርክሮችና ችሎቶች ብሎም የፍርድ ሂደት ውስጥም ቢሆን ጋብቻችን ስለመፍረሱ የሚያስረዱ በርካታ ሰነዶች ቀርበው ሳለ፤ የንብረት ክፍፍል ስለመደረጉም ህጋዊ ማስረጃዎች ቀርበው እያለ የተሰጠው ፍርድ ከምን መረጃ የመነጨ ነው ሲሉም ይጠይቃሉ። ከዚህም በተጨማሪ በፍርድ ቤት ሲቀርቡ የነበሩ ምስክሮች ጥቅም ፈላጊ የሆነው ዳዊት ዘመረ የተባለ ልጃቸውና ሌላኛው ደግሞ ስለ ጉዳዩ ምንም መረጃ የሌለውና አሜሪካን አገር 30 ዓመት በላይ የኖረ ግለሰብ ሲሆን በእነዚህ ላይም ተቃውሞ ባሰማም ሰሚ አጣሁ ባይ ናቸው። ሌላው ደግሞ የእኔን አምስት ምስክሮች ለመስማትም ፈቃደኛ አለመሆኑ ፍትህ ወደየት እየሄደ ነው ስል እንድጠይቅ፤ በአገሬም የፍትህ ሥርዓት ላይ ትልቅ ጥያቄ እንዳነሳ ያደርገኛል ይላሉ። በተለይም የማስረጃ ምዘና በአግባቡ ከማየት አኳያ ትልቅ በደል እንደተፈፀመብኝ አገርና መንግስት ይወቅልኝ ሲሉ ቅሬታቸውን ያሰማሉ።

**የአቶ ዘመረ ጥያቄዎች**

ንብረት በውል ስለመከፋፈላችን በሁለታችን ወገን ሽማግሌዎች በፊርማቸው አረጋግጠዋል። በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ ሁለት ቤት ቁጥር 405 ውጪ ሁሉንም ስለመከፋፈላችን በፊርማችን አረጋግጠን ሳለን እንደምን ዳግም ንብረት ተከፋፈሉ ይባላል፤ ለመሆኑ የእኔን ድርሻ ለሁለተኛ ጊዜ ሳካፍል ለህሊናስ እንደምን መፍረድ ይቻላል የሚለውን ጥያቄ ያነሳሉ። ሌላኛው ጥያቄያቸው ሁለታችንም ያላገባ ሰርተፍኬት ለፍርድ ቤት አቅርበን አልተፋታችሁም ሲባል ግራ አያጋባም ሲሉም ይጠይቃሉ። በባንክ ያለውን ገንዘብም ባንኮች ራሳቸው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ መሰረት ማከፋፈላቸውን እየተገለፀ እንዴት ድጋሚ የንብረት ክፍል ይደረግ ይባላል ሲሉም በአግራሞት ይጠይቃሉ። በዚህ የፍርድ ሂደት ሀቄን አጥቻለሁ፤ ፍርድ ተዛብቶብኛል፤ ሰበርም ቅስሜን ሰብሮኛል ሲሉ ሂደቱ የሚያሳምም ፍርዱም ሚዛን ያልጠበቀ ስለመሆኑ ይናገራሉ።

**የቦሌ ክፍለ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤትም፤ የ1965 ዓ.ም ጋብቻ ስለመፍረሱ እና የእርቅ ስምምነቱ ወደነበረበት እንደማይመልሰው አረጋገጠ። ሆኖም እርቅ ሥምምነት ሲፈረም አዲስ ጋብቻ እንደተፈፀመ ይቆጠራል ይልና፤ ስለዚህ 2004 ህጋዊ ጋብቻ ከዛሬ ጀምሮ እንዲፈርስ ወስኛለሁ ሲል የ2004 ዓ.ም የተከናወነውን እርቅ ጋብቻ እያለ በመጥራት ብያኔ ሰጠ። በዚህ ጊዜ አቶ ዘመረ ለቦሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አሉ**



№ 135375

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

City Government Of Addis Ababa

ኢትዮጵያ - Ethiopia

Vital Statistics Registration Service

የመ.ቁ B/NM-2008-/1:2
File. No:

ያላገባ/ች የምስክር ወረቀት

Non-Marital Certificate

ሙሉ ስም አልማዝ አስፋው ዘወልዴ ፆታ ሴት

Full Name ALMAZ ASFAW ZEWOLDE Sex FEMALE

የትውልድ ቀን 21/11/1937 ዜግነት ኢትዮጵያዊት

Date of Birth 28/07/1945 Nationality ETHIOPIAN

የትውልድ ቦታ አዲስ አበባ

Place of Birth ADDIS ABABA

የእናት ስም አስካለ ወ/ፃዲቅ

Mother's Name ASKALE W/ZADIKE

መግለጫ ከ22/04/2003 ጀምሮ ያላገባች

Remark AFTER 31/12/2010 SINGLE

አድራሻ : አዲስ አበባ፣ቦሌ፣ ወረዳ02፣ የቤ/ቁ405


Address : Addis Ababa,Bole, Wereda:02 ,H.No:405

የተሰጠበት ቀን 25/07/2009

Issued Date 03/04/2017

የክብር መዝገብ ሹም

Officer of Civil Status



AwashBank

አባ/ፋ&ት.ዳ/0095/19

ጥር 16 ቀን 2011 ዓ.ም

ለ አቶ ዘመረ ጀማነህ

<u>አዲስ አበባ</u>

በቀን 1 ጥር 2011 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በወ/ሮ አልማዝ አስፋው እና በእርሶ መካከል በነበረው የቤተሰብ ክርክር በፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረት በሁለታችሁ ስም የተከፋፈለ መሆኑን በመጥቀስ ባንኩ ምን ያህል አክሲዮን እንዳከፋፈለ መረጃ እንዲሰጥዎት መጠየቅዎ ይታወሳል ።

በዚሁ መሠረት በቀን 14 ግንቦት 2004 ዓ.ም በከ/መ/ቁ 142607 በተላለፈው የፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲሁም በቀን 11 ሐምሌ 2004 በጋራ በፃፋችሁልን ማመልከቻ መሠረት ከነበረው 930 አክሲዮን በብር 930,155.57 (ዘጠኝ መቶ ሰላሳ ሺ. አንድ መቶ ሀምሳ አምስት ከ57/100) ከነበረው ትርፍ ብር 338,808.15 (ሦስት መቶ ሰላሳ ስምንት ሺ. ስምንት መቶ ስምንት ከ15/100) ጋር ወደ አክሲዮን ዞሮ በአጠቃላይ 1,286 አክሲዮኖች በብር 1,268,963.73 (አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ስልሳ ስምንት ሺ. ዘጠኝ መቶ ስልሳ ሦስት ከ73/100) እኩል የተካፈለ ሲሆን 634 አክሲዮኖች በብር 634,000.00( ስድስት መቶ ሰላሳ አራት ሺ.) ለ ወ/ሮ አልማዝ ያስተላለፍን መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

<u>**ከአዘጋጁ**</u>

የዝግጅት ክፍላችን ከዚህ የፍርድ ሂደት ጉዳይ ጋር ተያይዞ ለሚመጡና በመረጃና ማስረጃ የተደገፉ የሌላ ወገን ሐሳቦችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኑን ለመግለጽ ይወዳል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# "ዘመን ወለዱ አውሉ ነፋስ የሚዘራው እብቅ"

**"በቃሉ ትርጉም እንስማማ!"፤**

ንባበ መንገዳችንን የምንጀምረው በሃሳብ ላይ የሚደረግን ፍልሚያ አስመልክቶ ጥንታዊ የግሪክ ፈላስፎች እንደ መርህ የሚቀበሉትን አንድ የተለመደ አባባል በማስታወስ ይሆናል። እነዚህ ተጠቃሽ ፈላስፎች የአደባባይ ሙግታቸውን፣ የግለሰብ አታካራቸውንና ቡድናዊ የሃሳብ ፍልሚያዎቻቸውን ከመጀመራቸው አስቀድሞ፤ "ሃሳባችን እንዳይበታተን በመጀመሪያ በምንወያይባቸው የቃላት ትርጉም ላይ እንስማማ" የሚሉት ዘመን ዘለቅ ብሂል ነበራቸው ይባላል።

ቅዱስ መጽሐፍም እንዲሁ፤ "ሁለት ሃሳብ ያለውና የሚወላውል ሰው... አንዳች አያገኝም"፤ ምክንያቱም ሃሳቡን ማስከን ያልቻለ ሰው፤ "በነፋስ እንደሚገፋና እንደሚናወጥ የባሕር ማዕበል ይመሰላል (ያዕቆብ 1፡6 - 8) ይለናል። ስለዚህም፤ የዋናውን ርዕሰ ጉዳያችንን ሁለት ቃላት (አውሎ ነፋስ እና እብቅ የሚሉትን)፤ መዛግብተ ቃላቱ እንዴት እንደበየኗቸውና በዚህ ጽሑፍ ውስጥም ምንን ለማመልከት በውክልና እንደተመረጡ መደላድሉን ካሳመርን በኋላ ወደ ዋናው የዕለቱ ጉዳያችን ዘልቀን እንገባለን።

"አውሎ ነፋስ፡- ኩርፊት፣ ጠሮ፣ ጥቅል ነፋስ፣ አቧራን ወደ ሕዋ የሚበትን፣ ጉድፍ ይዞ የሚነሳ፣ በሰውና በንብረት ላይ ጉዳት የሚያደርስ ኃይለኛ ነፋስ" በማለት በይኖታል። በዘርፉ ባለሙያዎች ትነታኔ መሠረትም ነፋስ የሚመደበው በአራት ባህርያት ሲሆን አውሎ ነፋስ ላቅ ብሎ ከፍተኛውን ደረጃ ይይዛል። እናስታውሳቸው፤ ለምለም ነፋስ፡- ቀስ ብሎ የሚነፍስ ሰላማዊ ነፋስ፣ ልክስክስ ነፋስ፡- አቧራ ወደ ላይ አንስቶ ለትንሽ ደቂቃ ያህል ካንከባለለ በኋላ በቶሎ የሚሰክን፣ ወዝዋብ ነፋስ፡- ዝናብ ቀላቅሎ የሚነፍስ ነፋስ ተብለው ተደንግገዋል።

አራተኛው አውሎ ነፋስ (weird wind/Tornedo) እና እንደየሀገሩ በልዩ ልዩ ስያሜዎች የሚታወቀው ሞገደኛ የተፈጥሮ ክስተት ግን በኃይል እየተሽከረከረ የተለያዩ ቁሳቁሶችን፣ እንስሳትንና ሰዎችን ሳይቀር ወደ ሰማይ በማጎን ከፍተኛ የሕይወትና የንብረት ውድመት የሚያደርስ አደገኛ ነፋስ መሆኑን መዛግብተ ቃላቱና ምሁራት ፍቺውን አስታውቀውናል። ይህንን መሰሉን አውዳሚ አውሎ ነፋስ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ የጠቀሰው "አውራቂስ" በማለት ሲሆን አደገኛነቱን የገለጸውም ይጓዙበት የነበረውን ግዙፍ መርከብና ጭነቶችን እንደምን በታትኖ እንዳወደማቸው በሥዕላዊ ገለጻ በመተረክ ነው።

**የአውሉ ነፋስና የእብቅ ማንጸሪያዎች፤**

በአውሎ ነፋስ ለመመሰል የተሞከረውም ግራ ገብና "በረከተ መርገም" የሆኑብንን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ነው። የነገውን መተንበይ ቢቸግርም በዚህ ወቅት እንደምናስተውለው ቴክኖሎጂው ጡንቻውን አፈርጥሞ ዘር፣ ቀለም፣ ሃይማኖትና የጂኦግራፊ ክልል ሳይገድበው የዓለምን አዳሜና ሔዋኔ የሰው ዘሮችን በሙሉ በአንድ ቅርጫት ማጎሪያ ውስጥ ለመከተት አቅም ያገኘበት ጊዜ ይመስላል። በሌላ አገላለጽ እናብራራው ካልን ቴክኖሎጂው አራቅቆ ባመቻቸው ማኅበራዊ ሚዲያዎች አማካይነት ዓለማችን በጣታችን ጫፍ ላይ እንድታርፍ ግድ ብሏታል። በእብቅ ለመወከል የተፈለገው የዚሁ የማኅበራዊ ሚዲያ "የይዘት ምርትም" ምን ያህል የነገሮችን ሥርና መሠረት እያናጋ እጅግ የከፋ ጥፋት እያደረሰ እንዳለ ዕለት በዕለት እያስተዋልን ነው።

ይህንን ጽሑፍ የሚያነቡ የጋዜጣው ወዳጆችና ቤተሰቦች በመረጃና በ"ማዝናኛ" የሚፈርጇቸውን የየግል መሻታቸውን ለማሟላት ከዚህ ጽሑፍ ንባባቸው አስቀድሞ የእጅ ስልካቸውን ወይንም የኮምፒውተራቸውን ቁልፎች ለተለያዩ የግልና የጋራ ጉዳዮቻቸው መከወኛነት በጣቶቻቸው ሳይነካኩ እንዳልቀረ መገመቱ አይከብድም።

> **በአሸባሪዎች እኩይ ድርጊት የንጹሐን ደም እንደ ጎርፍ የሚፈሰውና በምስኪኖች ላብና ጥረት የተገኘ ሀብትና የመንግሥት ተቋማት እንዳልነበሩ ሆነው እንዲፈራርሱና እንዲዘረፉ የሚፈረድባቸው በአብዛኛው ከማሕበራዊው ሚዲያው አውድማ ላይ የሚታፈሱ እንክርዳድ ሃሳቦች በጨካኞች አናት ላይ ወጥተው ስለሚያሰክሯቸው ነው**

ቴክኖሎጂው አራቆ ባቀረበላት የመገናኛ ዘዴዎች አማካይነት ግዙፏ ዓለማችን ተኮማትራ ልክ እንደ አንድ የአተር ፍሬ አንሳ መዳፋችን ላይ ወድቃለች። ብዙዎቹ እንደ ሱስ ተጠናውቷቸው የገበሩለትን የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምና በመዳፋችን ውስጥ ስናሽሞነሙን የምንውለውን የእጃችንን ስልክ አገልግሎት በተመለከተ ረጋ ብለን ብናሰላስል ይህ አገላለጽ በሚገባ ግልጽ ይሆንልናል።

የእጅ ስልክን ጉዳይ ከጠቀስን አይቀር መራር ትዝብታችንን እንዲያለዝብልን ከጥቂት ዓመታት በፊት የግል ሲም ካርድ ለማግኘት የነበረውን ውጣ ውረድ አስታውሰን እንለፍ። የዛሬ ጀንበር አትስማንና አንዲት ሲም ካርድ ለማግኘት የመኪና ሊብሬ ወይንም የቤት ካርታ እንድናሲዝ በባለሥልጣኑ ኢትዮ ቴሌኮም (በቀድሞ ስሙ የኢትዮጵያ ቴሌኮሚዩኒኬሽን) መጠየቅ ግድ እንደነበር የደረስንበትና ጣጣውን የተጋፈጥን ዜጎች የምናስተውሰው ነው። የስልክ ቁጥር የምርጫ ፕሮቶኮል እንደነበርም አይዘነጋም። ለምሳሌ፡- በ20 እና በ21 የሚጀምሩ የስልክ ቁጥሮች በአክብሮት ይታደሉ የነበረው በሀብት ለከበሩ ነጋዴዎችና ኢንቨስተሮች፣ በሥልጣን ለመጠቁ፣ እጃቸውና የአንደበታቸው ምላስ ሹማምንቶቹንና ነጋዴዎቹን ለመደገፍ ለሚረዝሙ አቀባባይ ደላሎችና የዕለት እንጀራቸውን ከዚያው ከቴሌ ለሚያገኙ ግለሰብ የሥራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ነበር።

በ40 ቁጥር የሚጀምሩ የስልክ ቁጥሮች ደግሞ ለምሁራንና ለተመራማሪዎች በሚል መወሰኑና በዚህን መሰሉ ክፍፍል ምክንያትም ምን ያህል የተቋሙ አንዳንድ ሠራተኞች ራሳቸውን በሙስናና በማጭበርበር ውስጥ ዘፍቀው እንደነበር ያልመሸበት ትናንታችን ምስክር ነው። ይህን መሰሉን መራር ትዝታ ወደ ኋላ ዞር ብለን ስናስታውስ መገረም ብቻም ሳይሆን አምርረን ድህነታችንን እንድንጠየፍ ጭምር ግድ ይለናል፤ ስሜቱ ዛሬም ድረስ የለቀቀን አይመስልም።

ይህ ጸሐፊ የውጭ ሀገር ትምህርቱን አጠናቆ ወደ ሀገር ቤት በተመለሰበት ወቅት ለእጅ ስልኩ የሲም ካርድ ለማግኘት ያጋጠመው ውጣ ውረድና እንግልት የትራጌዲ ተውኔት ያህል እንደምን ስሜቱን እንዳኮመጠጠና በወቅቱ ይታይ በነበረው ብልሹ የአሰራር ዘዴ ምክንያትም ምን ያህል እንግልት እንደደረሰበት በግለ ታሪክ መጽሐፉ ውስጥ በዝርዝር ስለሚታወስ ወደፊት በግላጭ ይነበባል።

**ሀገራዊ ገመናችን ሲፈተሽ፤**

በአውሎ ነፋስ የመሰልነው የቴክኖሎጂው የዕድገት ሩጫ እንደ አትሌቶቻችን በሜትር ወይንም በኪሎ ሜትሮች በሚለካ ርቀት "ላብን አፍስሶ" የሚጠናቀቅ ውድድር እና ሪከርድ "ይሰበርበታል" ተብሎ የሚፎከርበት ጉዳይ አይደለም። በጭራሽ። ቴክኖሎጂው መሽቶ በነጋ ቁጥር በአስደማሚ ግኝቶች "እጃችንን በአፋችን ላይ እንድንጭን" የሚያስገድዱንን ብዙ የፈጠራ ግኝቶች ማምረቱን እያስተዋልን ነው። እርግጥ ነው ዘመኑ "ለቴክኖሎጂ ውጤቶች አጉራህ ጠናኝ" ብለን እንድንገብር በውዴታ ብቻ ሳይሆን በግዴታ ጭምር እንደተቆራኘን አይካድም። በአዎንታዊ አድናቆት የሚንቆለጳጳሰውንና አጃኢብ እያሰኘን የምንገረምበትን በረከቱን ለጊዜው አቆይተን ወደ አልተፈለገ የሕይወት አቅጣጫ ትውልዱን እየመራ ያለውን መርገምታዊ ጎኑን ብቻ ጫን ብለን ለመዳሰስ እንሞክራለን።

"በረከተ መርግም" ብለን ተንደርድረናልና፤ ከምንጊዜውም ይልቅ ዛሬ የቴክኖሎጂ አጠቃቀማችንን በተመለከተ "አሰሩን ከጥፍጡ" እንዴት መለየት እንደሚገባን ጊዜና ፋታ ሳንሰጥ መወያየት ያለብን ስለመሰለን ይህንን ዋና ርዕሰ ጉዳይ ለዛሬው ውይይት መርጠናል። ሀገራዊና ነባር ፈሊጣዊ ብሂላችን "ነፋስ ገባው" በማለት የሚገልጻቸው በርካታ ስሜቶችን ነው። "ነፋስ ገባው"፡- ሲባል ሆዱ ጎሸ፣ አቄመ፣ ፍቅር፣ አንድነትና ስምምነት አጣ፣ ተለያየ፣ ተጠፋፋ፣ ተቀያየመ ወዘተ." ማለት ነው። በአውሎ ነፋስ የመሰልነው የቴክኖሎጂ ግኝት የሆኑት የማሕበራዊ መድረኮችም ሀገራዊ ክፍተት ፈጥረው እንደምን "ነፋስ እንዳስገቡብን" ዝርዝር ጥናት ሳያስፈልገው በብዙ ማሳያዎች ማመላከት ይቻላል። ቀላል ማሳያ ሊሆን የሚችለው ግን ደጋግመን እንደገለጽነው በእጃችን መዳፍ ላይ አሳርፈን ስንግባባበት፣ ስንናቆርበትና ስንፋጅበት የምንውለውን ስልካችንን መጥቀሱ ብቻ በቂና ከበቂ በላይ ነው።

በአሸባሪዎች እኩይ ድርጊት የንጹሐን ደም እንደ ጎርፍ የሚፈሰውና በምስኪኖች ላብና ጥረት የተገኘ ሀብትና የመንግሥት ተቋማት እንዳልነበሩ ሆነው እንዲፈራርሱና እንዲዘረፉ የሚፈረድባቸው በአብዛኛው ከማሕበራዊው ሚዲያው አውድማ ላይ የሚታፈሱ እንክርዳድ ሃሳቦች በጨካኞች አናት ላይ ወጥተው ስለሚያሰክሯቸው ነው። የዘረኝነት እብቅና የጽንፈኝነት ገለባም ከመቼውም ዘመን ይልቅ በዚህ በእኛ ጀንበር እየተጫነ የሚበተነው በአውሎ ነፋስ በመሰልናቸው ቴክኖሎጂ ወለድ በሆኑ በርካታ ማሕበራዊ ሚዲያዎች አማካይነት መሆኑ ተደጋግሞ አቤቱታ ቀርቦበታል።

የሃይማኖት ተቋማት፣ መሪዎቻቸውና አገልጋዮቻቸው፣ የመንግሥት የሥራ መሪዎችና የበላዮች፣ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚዋረዱበትና ሰብዓዊ ክብራቸው ሳይቀር የሚንቋሸሸው ለዘመናት ከዳበሩት በጎ ማሕበራዊ እሴቶች ውጭ ባፈነገጠ መልኩ በሚሰራጩና እብቅ ይዘት ባላቸው መልእክቶች አማካይነት ነው። በጨለማ አስተሳሰብ የተጋረዱና ለክፋት ተልእኮ የተማማሉ እኩይ የማሕበራዊ ሚዲያ ጀብደኞች ስማቸውንና ማንነታቸውን እየለዋወጡ የሚዘሯቸው እብቅ አስተሳሰቦች በሀገር ላይ ያደረሱትና እያደረሱ ያሉት ጥፋቶች ከብዛታቸው የተነሳ በዋጋም ሆነ በመጠን የሚገመቱና የሚመዘኑ አይደሉም።

"ምታ ነጋሪት፤ ቀስቅስ ሠራዊት" የሚል መፈክር በማስተጋባት ቀን ከሌት በሚተጉ የማሕበራዊ ሚዲያ ሠልፈኞች አማካይነት ከግለሰብ እስከ ሀገር የደረሱት ጉዳቶች ምን ያህል ሊሆኑ እንደሚችሉ ተጠንተው ይፋ ቢደረጉ ለበጎነት ሳይቀር የምንጠቀምበትን ማሕበራዊ ሚዲያ "ሀራም" በማለት "በውጉዝ ከመ አሪዮስ" ውሳኔ ጭርሱኑ በተፋታነው ነበር። የአውሎ ነፋስ አናፋሾቹ እውነታነት በሌለውና በፈጠራ በተቀናበረ ታሪክ የምን ያህሉን ቤት እንዳፈረሱ፣ የምን ያህሎችን ስሜትና መንፈስ እንደሰበሩና እንዳኮላሹ፣ ምን ያህሎቹን ለመከራና ለስቃይ እንደዳረጉ "ቤቱ ይቁጠረው" ብለን ካላለፍን በስተቀር ነካክተን የምንዘልቀው አይደለም።

ድንጋዩን ዳቦ ነው፣ እሬቱን ወለላ ማር ነው፣ እርኩሱን ቅዱስ ነው የሚሉ "የእብቅ ሃሳብ ነጋዴዎች" በአንዳንድ ግለሰቦችና ቡድኖች ላይ የፈጸሙትን ሰይጣናዊ ተግባራት ብዙም ባይሆኑ ጥቂቶች በድፍረት አደባባይ እየወጡ ምስክርነት ሲሰጡ እያስተዋልን ነው። እብቅ ገለባ ዐይን ውስጥ ሲገባ እንደሚያስነባ ሁሉ በእብቅ የመሰልናቸው የማሕበራዊ ሚዲያ ልጥፎች የሚያስለቅሱት ሥጋዊ ዐይንን ብቻ ሳይሆን ነፍስና ስሜትንም ጭምር ነው።

የነፋስ ዓይነቶችን በተመለከተ ቀደም ብለን እንደዘረዘርነው ለሰስ ብሎ በሚነፍስ ነፋስ የሚመሰሉ ለምለም ሃሳቦችን ከማሕበራዊ ሚዲያዎች ላይ ማግኘት መቻሉ እርግጥ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አነፋፈስ ጤናማ መሆኑን መካድ ስለማይገባ የምናልፈው አመስግነን ነው። በአንጻሩ አቧራ በሚያጨሱ ልክስክስና ወዝባማ ነፋሳት የሚመሰሉ መልእክቶችና አውዳሚ ሃሳቦችም የተለመዱ የማሕበራዊ ሚዲያው ክስተቶች መሆናቸው የሚካድ አይደለም።

ጽሑፉን የምንጠቀልለው ጉዳዩ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ ተቋማት እንደሚከተለው አቤቱታ በማቅረብ ይሆናል። የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን በተመለከተ ሕጉ ጸድቆ ተግባር ላይ ይዋል ከተባለ ወራት ተቆጥረዋል። እስከ ዛሬ ሊተገበር ያልቻለበት ምክንያቱ ምንድን ነው? የሚታወቁ ግለሰቦችና ቡድኖች "እዩን፣ ለዩን፣ ስሙን" እያሉ አዋጅ እየለፈፉ እያየንና እየሰማን ሕጉ ራሱ ለምን "በሕግ አምላክ!" ለማለት አቅሙ ተልፈሰፈሰ? መልስ ያለው መልሱን ቢያሳውቀን፣ መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ያለልሆነውም "እምቢታውን በይፋ ቢገልጥልን" አውሎ ነፋሱ ቢያንገዳግደንና እብቁ ቢያስለቅሰንም ቁርጣችንን አውቀን "ተው ቻለው ሆዴ" እያልን በማንጎራጎር ቀኑን እንገፋ ነበር። እባካችሁ ሕዝባዊ እሪታችንን አድምጡልን። ሰላም ይሁን!

ኢኮኖሚ

# ንግድና ግብይት

# እነክሪፕቶከረንሲ - የዲጂታል ግብይቱ ፈተናዎች



**ዳናት ተስፋዬ**

ዓለም የደረሰበት የሥልጣኔ ደረጃ ነገሮችን ከማቅለል ባሻገር ሰዎች ስራ ላይ የሚያሳልፉትን ጊዜና ጉልበት የሚቀንስ ሆኗል። እንደማሳያም "በይነ መረብ" ሰዎች ሥራዎችን በቤታቸው ወይም ባሉበት ቦታ ሆነው መስራት የሚችሉበትን እድል ፈጥሯል። በቅርብ ጊዜ የወጡ ጥናቶች እንደሚያሳዩት 16 በመቶ የሚሆኑ የዓለማችን ድርጅቶች የበይነ መረብ ስራዎችን የሚያሰሩ ናቸው። እነዚህና መሰል የስራ አጋጣሚዎች የአኗኗር ስልትን ማዘመን፣ የተሻለ ገቢን ማስገኘትና ለሌሎች ማሕበራዊ ጉዳዮች በቂ ጊዜ ማግኘትን ጨምሮ ብዙ ጠቀሜታዎች ይኖራቸዋል።

የበይነ መረብ ፋይዳ በተለይ በኮቪድ ወቅት በሚገባ ታይቷል፤ ወቅቱ ከቤት አትውጡ ይባል የነበረበት እንደመሆኑ ስራና ሰራተኛ የተቆራረጡበት ወቅት ቢባል ማጋነን አይሆንም። በዚያ ወቅት ግን ምስጋና ለቴክኖሎጂ ከቤታቸው ሆነው ስራቸውን የሚያከናውኑ ጥቂት አልነበሩም። ስራ ማከናወኛው መንገድ ደግሞ በየነ መረብ ነበር። አንዳንድ ሰራተኞች ቤታቸው ስራቸውን እየሰሩ በበይነ መረብ አማካይነት ወደ ተቋማቸው ይልኩ ነበር።

ሰዎች ከቤት በማይወጡበት፣ ብዙዎች በከሰሩበት በዚያ ወቅት በይነ መረብ ተጠቃሚዎች ግን ትርፋማ ሆነው እንደነበር በወቅቱ ሲዘገብም ነበር።

በበይነ መረብ የሚከናወኑ ስራዎች የተለያየ ፋይዳዎች ያላቸው መሆኑ ቢታመንም፣ ተአማኒነታቸውና ቀጣይነታቸው አጠራጣሪ የሚሆኑባቸው አጋጣሚዎችም ይስተዋላሉ። አጠራጣሪ ብቻም ሳይሆን ሕገወጥ የሚሆኑበት ሁኔታም ጥቂት አይደለም። በሀገራችን በእዚህ አይነት መንገድ በተደረጉ ግብይቶች ብዙ ሰዎች ገንዘባቸውን አጥተዋል። ለመሆኑ እነዚህ ግብይቶች እንዴት ነው የሚሰሩት።

**ዲጂታል ገንዘብ**

ዘመናችን ካመጣቸው አበይት ክስተቶች መካከል የክሪፕቶከረንሲ ቴክኖሎጂ አንዱ ነው። ክሪፕቶከረንሲ በዋነኝነት ቢትኮይን የሚባለው የብሎክቼን ስርዓት የሚጠቀም ቴክኖሎጂ ሲሆን፤ ሳቶሺ ናካማቶ በሚባል ማንነቱ እስካሁን ድረስ በግልጽ ባልታወቀ ሰው አማካኝነት እ.ኤ.አ በ2008 የተፈጠረ ነው። በ2009 ደግሞ ገበያ ላይ ለሁሉም ሰው ተደራሽ መሆን በሚችል መልኩ የተለቀቀ ሲሆን፤ ራሱን በራሱ መቆጣጠር በሚያስችል መልኩ እንዲሰራ ተደርጎ የተሰራ የዲጂታል ገንዘብ ሥርዓት ነው። ይህም የሃርድ ከረንሲ ወይም የወረቀት ገንዘብን በመተካት ከንክኪ ውጪ የሆነ ምናባዊ የገንዘብ ሥርዓት የፈጠረ ሲሆን፤ በዓለማችን የገንዘብ ሥርዓት ላይ የራሱን ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከት የቻለ ቴክኖሎጂ ነው።

**ስለዲጂታል የገንዘብ ሥርዓት**

የዲጂታል የገንዘብ ሥርዓት በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረገውን የገንዘብ ልውውጥ ሥርዓት (ትራንዛክሽን) ለሚቆጣጠሩ ሰዎች ሥርዓቱ የሚሸልመው የተወሰነ ቢትኮይን ስላለ የኮምፒውተር እውቀት፣ የተሻለ አቅም ያለው ኮምፒውተር፣ የተሻለ የኤሌክትሪክ ኃይል እና የኢንተርኔት ፍጥነት ያለው ማንኛውም ሰው ቢትኮይኑን በመጠቀም ገንዘብ መስራት እንዲችል ተደርጓል።

አሜሪካ፣ አውሮፓ፣ ካናዳ፣ አውስትራሊያ፣ ፈረንሳይ፣ ጃፓን፣ እንግሊዝ፣ ስፔን፣ ሜክሲኮ እና ማዕከላዊ የአፍሪካ ሪፐብሊክ የቢትኮይን ሕጋዊ የገንዘብ ሥርዓት ከተፈቀደባቸው አገራት መካከል ሲጠቀሱ፤ በተቃራኒው ደግሞ ቻይና፣ ኢራቅ፣ አልጄሪያ፣ ሞሮኮ፣ ቱኒዚያ፣ ባንግላዴሽና ግብፅ ቢትኮይን በአገራቸው የመገበያያ ገንዘብ እንዳይሆን ከሚከለክሉ አገራት መካከል ይጠቀሳሉ።

በሀገራችን ደግሞ የቢትኮይን ጉዳይ ያሳሰበው ብሄራዊ ባንክ በዚህ ዲጂታል ግብይት መገበያየትም ሆነ ክፍያ መፈጸምን ሕገወጥ ሲል በቅርቡ መግለጫ አውጥቶበታል። ምናባዊ ገንዘብን ወይም ንብረትን ከግብይት ወይም ለክፍያ መጠቀም በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ እውቅና ያልተሰጠው ድርጊት መሆኑን በመግለጽ ሕብረተሰቡ ከዚህ አይነት ድርጊት ራሱን እንዲጠብቅ አስገንዝቧል፤ ይህን ድርጊት በሚፈጽሙት ላይም ሕጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ አስታውቋል።

የክሪፕቶከረንሲ ተጠቃሚዎች ትርፍ ከሚያገኙባቸው በርካታ መንገዶች መካከል፤ አንዳንድ ተቋማት ደምበኛን ለመሳብ በስጦታ መልክ ሲያበረክቱ ሲሆን፤ ሌሎች ደግሞ የክሪፕቶከረንሲን በየጊዜው የዋጋ ለውጥ ማሳየትን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ገዝተው በማስቀመጥና ሲወደድ በመሸጥ ነው።

**እነዚህን አይነት ድርጅቶች ከዚህ ቀደም በሚከተሉት የፒራሚድ ስሌት አሰራር ብዙዎችን በማጭበርበራቸው ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይሰሩ እገዳ የተጣለባቸው መሆኑ ይታወሳል**

የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉት፣ ክሪፕቶከረንሲ መንግሥት በጥሬ በሚያትመው ገንዘብ ምክንያት የሚፈጠረውን የዋጋ ግሽበት ለመከላከል የሚያግዝ መሆኑ እንደ መልካም አጋጣሚ የሚነሳ ሲሆን፤ በተቃራኒው ደግሞ የባንኮችን ሥራ መገዳደሩ እና የደሕንነት ስጋቶች መነሳታቸው እንደ መጥፎ ጎን የሚነሱበት ናቸው።

**የዲጂታል ገንዘብ ማጭበርበር**

ስለዲጂታል የገንዘብ ሥርዓት እንደሚሰራ ያህል ካየን፤ የዲጂታል/የክሪፕቶከረንሲ ማጭበርበር እንዴት እንደሚሰራ ለማየት እንሞክር። የዲጂታል ገንዘብ ሥርዓት ሥራው ብዙ ጊዜ በቡድን በተደራጁ ባለሙያዎች የሚሰራ ሲሆን፤ የፒራሚድ ሥርዓት ያለውና ከላይ ያሉት ሰዎች ከስራቸው ሰዎችን እያስገቡ ግብይቱን የሚያሳድጉበት ሂደት ነው። በዚህም ከስር የገባው ሰው ከሚፈጽመው ክፍያ በየደረጃው ከላይ ያሉ አባላት ገንዘብ እንዲያገኙ የሚደረግበት ሥርዓት ነው።

ይህም አሳማኝ ይሆን ዘንድ ማሕበራዊ የትስስር ገጽን የሚጠቀሙ ሲሆን፤ ለዚህ የተዘጋጁት ግለሰቦች ገንዘብ እንዴት እያገኙ እንደሆነና ሕይወታቸው እንዴት እየተቀየረ እንደሆነ በመተረክና በማስመሰል የተሳሳተ ተሞክሯቸውን ቪዲዮ በመስራት ሌሎችን ለማሳመን ይሞክራሉ። በተጨማሪም ገንዘብ ከፍለው ለገቡ አዳዲስ አባላት ከከፈሉት ገንዘብ በጥቂቱ በወኪሎቻቸው በኩል ወደ የባንክ አካውንታቸው እንዲገባ በማድረግ በጉዳዩ ላይ ያላቸው እምነት እንዲጨምርና ሌሎች ሰዎችንም ወደ ሥርዓቱ እንዲያስገቡ የሚያደርጉበትም ሁኔታ እንዳለ ማንነታቸው እንዲገለጽ ያልፈለጉ የጉዳዩ ሰለባ የሆኑ ምንጮች ይገልጻሉ።

በቅርቡ ደግሞ ፊያስ (fias777.com) በሚል ስያሜ በሚጠራ ድርጅት ምክንያት ብዙዎች ለኪሳራ መዳረጋቸው እንዲሁም ተስፋ መቁረጥ ደረጃ መድረሳቸው እየተሰማ ይገኛል። እኛም ከዚሁ ላይ በማተኮር፣ ፊያስ ምንድነው? ምን አይነት የገበያ ሥርዓት ነው? ማን ማንን ተጠቃሚ ያደርጋል? እንዲሁም ተአማኒነቱስ ምን ያህል ነው? የሚሉ ተያያዥ ጥያቄዎችን በዚህ ጽሁፍ ውስጥ ለመዳሰስ እንሞክራለን።

"ኢትዮጵያ ቼክ" በማሕበራዊ ሚዲያ እና በመደበኛ ሚዲያዎች የሚቀርቡ ሀሰተኛ መረጃዎችን የሚያጣራ ዌብሳይት ፊያስ በተባለው ድርጅት ላይ ባደረገው ማጣራት፤ ድርጅቱ ራሱን የኮሚሽን ስራ የሚሰራ የማስታወቂያ ድርጅት ብሎ እንደሚጠራና አሰራሩም ቀላልና ክሊክ ማድረግን (መጠቆምን) ብቻ የሚጠይቅ፣ አባላቱም የሚሰጣቸው የስራ ብዛትና የሚያገኙት የገቢ መጠን እንደየደረጃው እንደሚለያይ ከቪ.አይ.ፒ ዜሮ (0) እስከ ቪ.አይ.ፒ አምስት (5) የደረጃ አይነቶች እንዳሉ ያብራራል።

ለምሳሌ፣ በቪ.አይ.ፒ 4 ደረጃ የሚገኝ አባል በቀን ውስጥ ከሚሰጡት 17 ስራዎች በአንዱ 18 ብር በመሰብሰብ በቀን 306 በወር ደግሞ 9ሺህ 180 ብር ማግኘት የሚያስችል መሆኑን ድርጅቱ ያስረዳል። በተጨማሪም ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ 2 ሚሊዮን የሚሆኑ ተጠቃሚዎች እንዳሉት የሚገልጽ ሲሆን፤ በሕዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት እንዳገኘም ይጠቁማል።

"ኢትዮጵያ ቼክ" ባደረገው ማጣራት ግን ድርጅቱ ስለ አሰራሩ ከገለጸው በተቃራኒ ሆኖ ነው የተገኘው። ድርጅቱ እንደ QuestNet እና Tiens የፒራሚድ ስሌት ያለው አሰራር እንደሚጠቀም «ኢትዮጵያ ቼክ» አረጋግጧል። እነዚህን አይነት ድርጅቶች ከዚህ ቀደም በሚከተሉት የፒራሚድ ስሌት አሰራር ብዙዎችን በማጭበርበራቸው ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ እንዳይሰሩ እገዳ የተጣለባቸው መሆኑ ይታወሳል።

የፒራሚድ ንግድ ስሌት የሚባለው አንድ ሰው በስሩ ብዙ ሰዎችን በማስገባት እነርሱም ሌሎች ሰዎችን እንዲሁ በስራቸው በማስገባት ሰንሰለቱ የሚቀጥልበት አሰራር ነው። በዚህ ሰንሰለት ውስጥ ደግሞ ከላይ ያሉት አባላት ተጠቃሚ ሲሆኑ፤ ብዙዎች ግን ተጭበርብረው ይቀራሉ። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ቼክ የድርጅቱ አባላት የሆኑ ሰዎችን አነጋግሮ ባገኘው መረጃ መሰረት ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ምዝገባም ሆነ ቢሮ እንደሌለው አረጋግጧል፤ ከዚህም አባላቱ ባለቤቶቹን የማወቅ እና የመጠየቅ መብት እንደሌላቸው መረዳት ይቻላል። ምንም እንኳን ድርጅቱ ኢትዮጵያ ውስጥ ምዝገባ አካሂጃለሁ ሕጋዊ ነኝ ቢልም፤ በንግድ ሚኒስቴር የንግድ ምዝገባ ጽ/ቤት ግን እንዳልተመዘገበ ኢትዮጵያ ቼክ ማጣራቱን ይገልጻል።

ከኢትዮጵያ ቼክ በተጨማሪም የማጭበርበር ድርጊቶችን ከሚከታተሉት አንዱ የሆነው ScamAdvisor ስለ ፊያስ ባደረገው ማጣራት ድርጅቱ ተዓማኒነቱ በጣም የወረደ መሆኑንና ማጭበርበር ሊሆን እንደሚችል፤ እንዲሁም ይህንን ዌብሳይት በሚጠቀሙበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ያሳስባል።

በአንድ ወቅት ፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት በሰራው ዘገባ ላይ እንዳመለከተው፤ በቲያንስ /Tiens/ አማካኝነት ሲተገበር የነበረው የአጋዥ ምግቦች የፒራሚድ ንግድ በ2008 ዓ.ም እገዳ ተጥሎበት ተቋርጦ ነበር። ሆኖም ግን ከ3 ዓመታት በኋላ ይህ አይነት የንግድ ስልት በ2011 መጨረሻ በድጋሚ ተመልሷል። ቲያንስ የተባለው ድርጅት አጋዥ ምግቦችን የሚሸጥ የነበረ ሲሆን፤ ሕገወጥ በሆነው የፒራሚድ ስልት በመጠቀሙ እና 200ሺህ የሚሆኑ አባላቱን አክስሮ በ2008 ዓ.ም ከተቋረጠ በኋላ ዳግም በ2011 ዓ.ም "ሪል ራይዝ ትሬዲንግ" በተባለው ጅምላ አከፋፋይ እና የችርቻሮ አከፋፋይ በሆነው በዊዝደም ኢምፓየር አማካኝነት ወደ ንግድ ሥርዓቱ መመለሱን ዘገባው ያስረዳል። ዊዝደም ኢምፓየር የተባለው ድርጅት የተባለውን አይነት ፒራሚዳዊ የንግድ ስልት እንደማይጠቀምና ከቲያንስ (Tiens) ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌለው ቢያሳውቅም፤ የተሰበሰቡት ማስረጃዎች ግን ይህንን ውድቅ የሚያደርጉ ሆነው ተገኝተዋል።

እነዚህ ከላይ የተመለከትናቸው ማሳያዎች እንደሚያሳዩት እንደ ፊያስ ያሉ የክሪፕቶከረንሲ ወይም የመስመር ላይ ስራዎች ተዓማኒነታቸው እጅግ አጠያያቂ በመሆኑ ሰዎች አባል ከመሆናቸው ወይም ስራውን ከመጀመራቸው በፊት አስፈላጊውን ማጣራት እንዲያደርጉ እና ራሳቸውን ከመጭበርበር ድርጊቶች እንዲከላከሉ ለመጠቆም እንወዳለን። ይሄም "ቀድሞ ነበር እንጂ መጥኖ መደቆስ አሁን ምን ያደርጋል ድስት ጥዶ ማልቀስ!" የሚለውን ተረት በራስ ላይ ከመተረት የሚታደግ አስፈላጊ ጥንቃቄ ነው።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ትዝብት

## የትምህርት ደረጃ የማይጠይቅ ማራኪ ደሞዝ

**ዋሰልኝ አየለ**

ልብ ብለን አናስተውልም እንጂ አንድ ነገር ውሸት መሆኑን ለመጠርጠር ብዙ አመላካች ነገሮች አሉ። ለምሳሌ በማሕበራዊ ገጾች ላይ ‹‹ፎቶ ሾፕ›› ተሰርቶ የሀሰት ዜናዎች ይሰራጫሉ። ልብ ብለን ካስተዋልን ግን አገላለጻቸው ተቋማዊ አይደለም። ምንም እንኳን በትክክል አስመስለው የሚያቀናብሩ ቢኖሩም አብዛኞቹ ግን የሚያስነቁ ናቸው። አንድ ምሳሌ ልጥቀስና ወደ ዋናው ትዝብቴ አልፋለሁ።

በአንድ ወቅት (ከ6ኛው አገር አቀፍ ምርጫ በፊት) ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው መሾማቸውን የሚያሳይ ደብዳቤ ማሕበራዊ ገጾች ላይ መዘዋወር ጀመረ። የሀሰት ዜናዎችን በማጣራት የሚታወቀው ጋዜጠኛ ኤሊያስ መሰረት አንድ ነገር ጻፈ። ያንን የሀሰት ዜና ለማጣራት ማንንም መጠየቅ ሳያስፈልግ ‹‹በእነዚህ ነገሮች ማወቅ ይቻላል›› ብሎ ደብዳቤው ላይ ያሉ ስህተቶችን በቀስት እያመለከተ ዘረዘራቸው። አጻጻፉ ተቋማዊ ፕሮቶኮልን የተከተለ አልነበረም። እንደተባለውም ሀሰት ሆኖ ተገኘ።

የዛሬ ትዝብቴ ስለሀሰተኛ የአሰሪና ሰራተኛ አገናኝ አካላት ነው። ወቅቱ የዩኒቨርሲቲ ተመራቂዎች ወደ አዲስ አበባ እየመጡ የሥራ ማስታወቂያዎችን የሚያዩበት ስለሆነ ችግሩ ጎልቶ ይታያል። በዚሁ ጉዳይ ላይ ከዚህ በፊትም ብዙ ትዝብቶች እንደነበሩ አስታውሳለሁ። በቅርቡ የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን በዚሁ ጉዳይ ላይ የሰራውን ዜና አይቼ ነው የችግሩ አሳሳቢነት ያስፈራኝ።

እንዲህ አይነት ዘገባዎች መደበኛ በሆነው ራስን በማስተዋወቅ መንገድ መሰራት ስለማይችሉ ጋዜጠኛው ሥራ ፈላጊ መስሎ ነው ምርመራውን የጀመረ። ዝርዝሩ ይቅርና መጨረሻ ላይ ግን አድራሻቸውን አጠፉ፤ ሀሰተኛ መሆናቸው ተረጋገጠ ማለት ነው።

እነዚህ ሀሰተኛ አሰሪና ሰራተኛ አገናኝ አካላት ሀሰተኛ መሆናቸውን የጠረጠርኩት በማስታወቂያቸው ነበር። ማስታወቂያቸው ግልጽ አድራሻ የለውም። ሕጋዊ የሆኑት ግልጽ አድራሻ ያስቀምጣሉ። ያሉበትን ቦታ ብቻ ሳይሆን ቦታውን ለማግኘት የሚያግዙ በአካባቢው ያሉ ታዋቂ ማጣቀሻዎችን ይጠቀማሉ። ያሉበትን ሕንጻ ስም ጠቅሰው፤ ስንተኛ ፎቅ ላይ እንደሆነ እና ቢሮ ቁጥር ስንት እንደሆነ ያስቀምጣሉ።

የሀሰተኞቹ ግን እነዚህን ነገሮች አያስቀምጡም። አራት ኪሎ ወይም መገናኛ መሆኑን ብቻ ይገልጻሉ። ከቶታል ዝቅ ብሎ ወይም ከፍ ብሎ የሚል ግልጽ ያልሆነ ነገር ይገልጻሉ። ከዚያ ውጭ ስልክ ነው የሚያስቀምጡት። ሥራ ፈላጊው አካል ስልክ ደውሎ ይገናኛሉ ማለት ነው።

ሌላው ማስታወቂያው ላይ የሚገለጸው ደግሞ ግልጽ ያልሆነ የደሞዝ አገላለጽ ነው። በደፈናው ማራኪ ይላል። ‹‹በድርጅቱ ስኬል መሰረት›› ወይም ‹‹በስምምነት›› ማለት የተለመደ ነበር። ማራኪ ማለት ግን ምን እንደሆነ አይታወቅም።

ሌላው አስቂኙ ነገር ‹‹የትምህር ደረጃ አይጠይቅም›› የሚሉት ነገር ነው። እውነት አሁን በዚህ ዘመን ቢያንስ መጻፍና ማንበብ እንኳን የማይጠይቅ የሥራ ዘርፍ አለ? ሌላው አስገራሚ ነገር አንዳንዶቹ ላይ ‹‹የትምህርት ደረጃ አይጠይቅም›› ለተባለው ሥራ እስከ 6,000 ብር ደሞዝ ይጠቀሳል። ዲግሪ እና ማስተርስ ለሚጠይቁ የሥራ መደቦች የማይከፈል ብር ምንም የትምህርት ደረጃ ለማይጠይቅ ሥራ እንዴት ተገኘ? ምናልባት ምንም የትምህርት ደረጃ የማይጠይቅ የቤት ሰራተኝነት ነው እንበል፤ ስድስት ሺህ ብር የሚከፈላት የቤት ሰራተኛ አለች?

ችግራችን አመክንዮ(ሎጂክ) የሚባል ነገር ልብ አንልም። በዚያ ላይ ‹‹የጨነቀው እርጉዝ ያገባል›› እንዲሉ ሥራ ፈላጊዎች ሲጨንቃቸው እነዚህን ነገሮች ልብ አይሉም። ለትራንስፖርት ተብሎ ከምትሰጣቸው ገንዘብ ላይ ነው ለእነዚህ ሀሰተኛ ደላሎች የሚከፍሉት።

ማስታወቂያዎቹ ልጆቹን ለማጭበርበር የማይጠቀሙት ዘዴ የለም። የሚጠቀሰው ስድስት ሺህ ብር ደሞዝ የተጣራ እና እጃቸው ላይ የሚደርስ መሆኑንም ይገልጻሉ። የሚፈለገው የሰው ብዛት ደግሞ እስከ 200 ይደርሳል። ይህን ያደረጉበት ምክንያት፤ የብዙ ሥራ ፈላጊዎች ስጋት የሚፈለገው ሰው ስንት ይሆን የሚል መሆኑን ስለሚያውቁ ነው። ምክንያቱም ህጋዊ ማስታወቂያዎች ሲወጡ በብዛት አንድ ሰው ብቻ፣ ግፋ ቢል እስከ ሦስት በጣም ከበዛ ደግሞ እስከ 10 ባለው ነው። ባንኮች እና አንዳንድ የፋይናንስ ተቋማት ብዛት ያለው ሰው እንደሚፈልጉ ቢታወቅም እነርሱ ግን በእንዲህ አይነት ደላላ አይደለም ሰራተኛ የሚቀጥሩት።

እንዲያው ግን ምንም የትምህርት ደረጃ የሌላቸው 200 ሰራተኞች የሚቀጥር ተቋም ይኖር ይሆን? ምናልባት ሥራው በተማረ ሰው መሰራት የማይችል ይሆን?

የትምህርት ደረጃ አይጠይቅም የሚሉበት ምክንያት ሁሉም እንድ መዘገብ ነው። አንዳንዱ የተማረበት የትምህርት ክፍል እንዳይገድበው፣ ሌላው ደግሞ የትምህርት ደረጃው እንዳይገድበው ማለት ነው።

የትምህርት ደረጃ አይጠይቅም ማለት መጻፍና ማንበብ የማይችልም ሊሆን ይችላል ማለት ነው። እንዲህ ከሆነ ታዲያ ማስታወቂያውን እንዴት ሊያነበው ይችላል? ስለዚህ በጽሑፍ ማስታወቂያ ሳይሆን በየአካባቢው እየዞረ በጡሩንባ ነበር ማስነገር የነበረበት።

ያልገባኝ ነገር አመዘጋገቡ ነው። ለምሳሌ የትምህርት ደረጃ የሚጠይቁት ላይ የትምህርት ማስረጃ እየታየ ይመዘገባል። ሥራው የግድ ያልተማረ ከሆነ የሚፈልገው ያልተማረ መሆኑን እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? ሥራውን ለማግኘት ሲሉ የትምህርት ማስረጃቸውን እየደበቁ ‹‹ኧረ እኔ ‹‹ሀ ሁ እንኳን ያልቆጠርኩ ጥሩ መሃይም ነኝ›› ሊሉ ይችላሉ። ታዲያ ያልተማሩ መሆናቸውን እንዴት ነው ማረጋገጥ የሚቻለው? ፈተናውስ እንዴት ይሆን?

እስኪ ፈተናውን ልገምት። የመፈተኛ አዳራሹ ውስጥ ትልቅ ሰሌዳ ወይም ስክሪን ይቀመጣል። ሰሌዳው ወይም ስክሪኑ ላይ ‹‹ገ›› ፊደል በትልቁ ትጻፋለች። ተፈታኙ ‹‹ይቺ ምንድናት?›› ተብሎ ይጠየቃል። ሆሄ መሆኗ ቀርቶ ‹‹ከዘራ ናት›› ካለ ፈተናውን ያልፋል ማለት ነው።

ቀልዱ ቀልድ ነው፤ እንዲህ አይነት ግልጽ ማጭበርበሪያዎችን ግን ሕግ ሊቆጣጠራቸው ይገባል። እንዲህ አይነት ማጭበርበሪያ እየተጠቀሙ ከተማሪዎች ላይ ለመመዝገቢያ እስከ 400 ብር ድረስ ይቀበላሉ። ያንኑ ማስታወቂያ በብዙ ቦታዎች ላይ ይለጥፉታል። ሁለ ነገሩ ተመሳሳይ ነው። ግልጽ አድራሻና ግልጽ የሥራ መደብ ወይም የትምህርት ደረጃ እስካልተቀመጠለት ድረስ ሥራ ፈላጊዎች ባገኙበት ቦታ ሁሉ ሌላ ማስታወቂያ ነው የሚመስላቸው። በዚያ ላይ አድራሻዎቻቸውን ይቀያይራሉ።

እነዚህ ሕገ ወጥ ደላሎች ሕሊናቸውን የሸጡ ስለሆኑ ‹‹ሥራ ፈላጊዎች አያሳዝኗቸውም?›› ብሎ መጠየቅ የዋህነት ነው። መፍትሔው እንዲህ አይነት አጭበርባሪዎችን መንግሥት ተከታትሎ እርምጃ ቢወስድባቸው ነው። ምንም እንኳን አድራሻቸውን እየቀያየሩ ቢያስቸግሩም ከታሰበበት ግን እንኳን እነዚህ የሽብር ድርጊት ለመፈጸም የሚንቀሳቀሱትም አምልጠው አልቀሩም።

እስከዚያ ድረስ ግን ጥንቃቄ ማድረግ ያለባቸው ሥራ ፈላጊዎች ናቸው። ምንም እንኳን በእነርሱ ቦታ ሆኖ ሲታይ ከባድ ቢሆንም በማንም አጭበርባሪ ግን መታለል የለባቸውም። ግልጽ አድራሻ ማየት አለባቸው። አብዛኞቹ ሕጋዊ ኤጀንሲዎችም ብር አይቀበሉም፤ ብር የሚቀበሉት ሥራ ፈላጊው ሲቀጠር ነው። ከአሰሪው ጋር ውል ስላላቸው ከሰራተኛው የመጀመሪያ ደሞዝ ላይ ይቆርጣሉ፤ ይህን የሚያደርጉት በሰራተኛው ፈቃድ እና ስምምነት ነው።

ከዚህ ውጭ ያሉት አገናኝ ኤጀንሲዎች ላይ ሥራ ፈላጊዎች ልብ ማለትና ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል!

# ዓለም አቀፍ



## ከፍተኛ ወጪ የወጣበት የኬንያ ምርጫ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ፕሬዚዳንት ኬንያታ በሕገ መንግሥቱ መሰረት የሁለተኛውና የመጨረሻው የአምስት ዓመት የሥልጣን ዘመናቸው ማብቃቱን ተከትሎ ሥልጣናቸውን ለቀጣዩ ፕሬዚዳንት ያስረክባሉ።

ምክትላቸው ዊልያም ሩቶ እርሳቸውን ለመተካት ቢፈልጉም ኡሁሩ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር እና በአንድ ወቅት ተቀናቃኛቸው የነበሩትን ራይላ ኦዲንጋን እየደገፉ ነው።

የሥልጣን ዘመናቸው የተጠናቀቀው ፕሬዚዳንት ኡሁሩ ኬንያታ በማዕከላዊ ኬንያ ውስጥ ባለችው የትውልድ ስፍራቸው ኪያምቡ በሚገኝ የምርጫ ጣቢያ ድምጽ ሰጥተዋል።

ፕሬዚዳንት ኬንያታ ድምጻቸውን ከሰጡ በኋላ ለጋዜጠኞች እንደተናገሩት “ይህ ምርጫ ነፃ እና ፍትሃዊ ይሆናል ብዬ አምናለሁ፣ የምርጫው ሂደትም የተቃና ነበር” ብለዋል።

ምርጫው አራት ዕጩዎች ለፕሬዚዳንትነት የሚፎካከሩበት ሲሆን፣ በተለይ በምክትል ፕሬዚዳንቱ ዊሊያም ሩቶና በቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ራይላ ኦዲንጋ በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ዋነኛ ተፎካካሪዎች ነበሩ።

የኬንያ ምርጫ ከሁሉ የተለየ የሚሆነው በዓለም ከፍተኛ ገንዘብ ካስወጡ ምርጫዎች መካከል አንዱ መሆኑ ጭምር ነው።

ከ22 ሚሊዮን በላይ መራጮች የተመዘገቡ ሲሆን፣ ለመምረጥ ብቁ ከሆኑ ከ5 ኬንያውያን 4ቱ በመራጭነት መመዝገባቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

ለምርጫው የተመደበው ገንዘብ 400 ሚሊዮን ዶላር ይጠጋል። በዚህም ለእያንዳንዱ መራጭ ከ17 ዶላር ወጪ ይደረጋል ማለት ነው። ይህም በአሜሪካ እና በዩናይትድ ኪንግደም ከተመደበው ገንዘብ ከፍተኛው ነው።

በኢትዮጵያ ባለፈው ዓመት በተካሄደው ስድስተኛው አገራዊ ምርጫ የተመደበው ገንዘብ አንድ መቶ ሚሊዮን ዶላር እንኳን አይሞላም ነበር። ከዚህ አንጻር የኬንያው ከኢትዮጵያ ምርጫ ከሶስት እጥፍ በላይ ከፍተኛ ወጪ ያስወጣ ምርጫ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ከ22 ሚሊዮን በላይ መራጮች የተመዘገቡ ሲሆን፣ ለመምረጥ ብቁ ከሆኑ ከ5 ኬንያውያን 4ቱ በመራጭነት ተመዝግበዋል።

ለምርጫው የተመደበው ገንዘብ ከ383 ሚሊዮን ዶላር በላይ ነው። በዚህም ለእያንዳንዱ መራጭ 17 ዶላር ወጪ ይደረጋል ማለት ነው። ይህም በአሜሪካ እና በዩናይትድ ኪንግደም ከተመደበው ገንዘብ ከፍተኛው ነው።

## ትራምፕ የኤፍቢአይ ወኪሎች መኖሪያ ቤታቸውን እንደፈተሹ ተናገሩ



የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ዶናልድ ትራምፕ ፍሎሪዳ የሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በኤፍቢአይ አባላት መከበቡንና ካዝናቸው መሰበሩን ተናገሩ።

ትራምፕ በሰጡት መግለጫ በፓልም ቢች የሚገኘው ማር-ኤ-ላጎ በተባለው ቤታቸውን “በርካታ የኤፍቢአይ ወኪሎች ተገኝተዋል” ብለዋል።

ፍተሻው ከትራምፕ የመንግሥታዊ ሰነዶች አያያዝ ጋር በተገናኘ ነው ተብሏል።

ትራምፕ እአአ በ2024 ለሦስተኛ ጊዜ የፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ዕጩ ሆነው ለመቅረብ ዝግጅት እያደረጉ ነው።

የቢቢሲ የአሜሪካ አጋር የሆነው ሲቢኤስ ኒውስ እንደዘገበው ሰኞ ዕለት ፍተሻው በተካሄደበት ወቅት ትራምፕ በኒውዮርክ ከተማ በሚገኘው ትራምፕ ታወር ነበሩ።

ትራምፕ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት ትብብር ማድረጋቸውን ገልጸው “በቤቴ ላይ የተደረገው ድንገተኛ ፍተሻ አላስፈላጊ ወይም ተገቢ አይደለም” ብለዋል።

በድጋሚ ለፕሬዚዳንትነት እንዳይወዳደሩ ለማድረግ “የሕግ ጥሰት መፈጸም” እና “የፍትህ ሥርዓቱን እንደመሳሪያ መጠቀም” ነው የተከናወነው ብለዋል።

“ካዝናዬን ጭምር ሰብረውታል ያሉት ትራምፕ በሚያሳዝን ሁኔታ አሜሪካ ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ደረጃ በሙስና ከተዘፈቁ አገራት አንዷ ሆናለች ሲሉ ተችተዋል።

ፕሬዝዳንታዊ መዝገቦችን የሚያስተዳድረው የዩናይትድ ስቴትስ ብሔራዊ ቤተ መዛግብት በየካቲት ወር ትራምፕ ኦፊሴላዊ ሰነዶችን ስለሚይዙበት መንገድ የፍትህ ክፍሉ ምርመራ እንዲያደርግ ጠይቋል።

ብሔራዊው ቤተ መዛግብቱ በምርመራው 15 ሳጥኖችን ማወሰዱን አስታውቋል። በፉልተን ካውንቲ ጆርጂያ የሚገኘው ዓቃቤ ህግ ትራምፕ እና አጋሮቻቸው በግዛቱ በ2020 ምርጫ ውጤቶች ላይ ጣልቃ ለመግባት ሞክረው እንደሆነ ለማወቅ እየመረመረ መሆኑን አስታውቋል።

የትራምፕ አማካሪ የሆኑ ግለሰብ ለሲቢኤስ እንደተናገሩት በፌዴራል ወኪሎች የተደረገው ፍተሻ ፕሬዚዳንታዊ መዛግብት ላይ ያተኮረ ነበር።

ስማቸው ያልተጠቀሰ የሕግ አስከባሪ ለሲቢኤስ እንደተናገሩት የትራምፕ ጠባቂዎች የፍተሻ ማዘዣው ቀደም ብሎ እንደደረሳቸው ተናግረዋል።

ይሁንና ትራምፕ ማዘዣው ሕጋዊ ያልሆነና ተገቢው ፊርማ ያልሰፈረበት ነው ሲሉ አጣጥለውታል።

ማህበራዊ

# ባለውለታዎቻችን

# የወታደራዊ ህክምና አመራር ቁንጮ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ከአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት ጀምሮ እስከ ወታደራዊ የደርግ መንግስት ድረስ ከአርባ አመት በላይ በውትድርናው መስክ አገራቸውን አገልግለዋል። በተለይ በሰሜንና ምስራቅ ጦር ግንባሮች የክፍለ ጦር ምክትል አዛዥና ዋና አዛዥ በመሆን አገራቸው የጣለችባቸውን ግዴታ ተፈጥሮ በቸረቻቸው ድንቅ ስጦታ በብቃት ተወጥተዋል። ከጦር አዛዥነታቸው በበለጠ ደግሞ የኢትዮጵያን ሠራዊትና ቤተሰቡን ብሎም ውድ እናት አገራቸውን በወታደራዊ የሕክምና ባለሙያነት አገልግለዋል።

ከውትድርናው መስክ ባሻገርም በበጎ አድራጎት ስራዎችም ለአገራቸው ጉልህ አስተዋፅ አበርክተዋል። በተለይ ደግሞ ቀይ መስቀልን ከግማሽ ምእተ አመት በላይ በማገልገል የዜግነት ግዴታቸውን ተወጥተዋል። የኢትዮጵያ የህፃናት ልብ ህሙማን ማህበርን ከኮለኔል ዶክተር በላይ አበጋዝ ጋር በመሆን ከመሰረቱ በጎ አድራጊዎች ውስጥም አንዱ በመሆናቸው በበርካታ ኢትዮጵያውን ዘንድ ይታወቃሉ- ምርጥ፣ ፀባይ ሸጋውና በቅርቡ ህይወታቸው ያለፈው አንጋፋው የአገር ባለውለታ ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ።

ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ የተወለዱት በ1911 ዓ.ም በቀድሞው የሐረርጌ ክፍለ አገር ጅጅጋ አውራጅ ከአባታቸው ከባሻ ቢሻኔ እርጎዬና ከእናታቸው ወይዘሮ አለሚቱ በዳሾ ነው። አብዛኛውን የልጅነት ግዜያቸውን ያሳለፉትም እዛው በተወለዱበት ጅጅጋ አውራጃ ነው። እንደማንኛውም በግዜው እንደነበሩት ልጆች ቤተሰባቸውን በተለያዩ መንገዶች በማገዝ አድገዋል።

ገና በልጅነታቸው ጥሩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ የመናገር ችሎታ የነበራቸው ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ ከጣሊያን ወረራ በኋላ ለእንግሊዛውያን በአስተርጓሚነት ሰርተዋል። በ1939 በሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት/ በዛሬው የኢትጵያ ወታደራዊ አካዳሚ/ የ12ኛ ኮርስ ተወዳዳሪ እጩ መኮንን ሆነው ወደ ውትድርናው ዓለም በመቀላቀል ወታደራዊ ስልጠና ወስደው ከኮርሳቸው በመወዳደር ከእጩ መኮንኖች በወታደራዊ ትምህርት ችሎታቸው አንደኛ ሆነው አጠናቀዋል።

በሆለታ ገነት ጦር ትምህርት ቤት በነበራቸው ቆይታ የውትድርናን ትምህርት በላቀ ውጤት አንደኛ ሆነው በማጠናቀቃቸው ወደ አሜሪካ አቅንተው ፎርት ሊበን ዎርዝ ካንሳስ ግዛት በሚገኘው የጦር አካዳሚ የወታደራዊ ጥበብ ተምረው በማዕረግ ተመርቀዋል። ተፈጥሯዊ እውቀታቸው፣ አንድን ነገር ለማወቅ ጉጉ መሆናቸውና ጉብዝናቸው ተጨምሮበት ትምህርታቸውን በጥሩ ውጤት ለማጠናቀቅ አስችሏቸዋል።

ከአሜሪካ የወታደራዊ ሳይንስ ትምህርት ቆይታቸው በኋላ ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ ወደ አገራቸው በመመለስ፤ በቅድሚያ የ9ኛ እግረኛ ብርጌድ አዛዥና እንደዚሁም የደቡብ ክፍለ አገራት አስተዳዳሪ በመሆን ለሦስት ዓመታት ያህል አገልግለዋል። ከዛም በ1961 ዓ.ም ወደ ኤርትራ ክ/ሃገር አሥመራ በመዛወር በዚያ ይገኝ የነበረውን ሁለተኛ ዋልያ እግረኛ ክፍለ ጦር በምክትል አዛዥነት ለአራት ዓመታት መርተዋል።

በቀድሞው የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት ለሰላሳ ዓመት ያገለገሉት፤ በሞያቸው ታንከኛ የነበሩትና በአንድ ወቅት ከብርጋዴር ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ ጋር አብሮ የመስራት አጋጣሚ የተፈጠረላቸው ብርጋዴር ጄነራል ዋስይሁን ንጋቱ ሲናገሩ ‹‹በ1964 ዓ.ም ከኦጋዴን ተዛውሬ አስመራ ስሄድ ከብርጋዴር ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ ጋር ተገናኝቼ የመስራት አጋጣሚ ተፍጥሮልኛል። በወቅቱ እርሳቸው የሁለተኛ ዋልያ እግረኛ ክፍለ ጦር ምክትል አዛዥ የነበሩ ሲሆን እኔ ደግሞ የዚሁ ክፍለጦር የታንክ ሻምበል አዛዥ ነበርኩ። በኤርትራ ውስጥ የነበረውን ጦርነትና ኦፕሬሽኑን የሚያካሂዱትና አስተዳናሩንም የሚመሩት እርሳቸው ነበሩ›› ብለዋል።

‹‹በግዜው ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ በትምህርት ችሎታቸው የላቁና በአሜሪካን ካንሳስ ግዛት ፎርት ሊበን ዎርዝ በሚገኘው የጦር ጥበብ አካዳሚ ገብተው ጠለቅ ያለ ወታደራዊ ጥበብ ቀስመው ወደአገራቸው የተመለሱና በባህሪያቸውም ጨዋና አርቆ አስተዋይ ነበሩ›› ሲሉ ብርጋዴር ጄነራል ዋስይሁን ንጋቱ መስክረዋል።

ከኤርትራ አሥመራ መልስ ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ በአዲስ አበባ ከተማ የአንደኛው ክፍለ ጦር ምክትል አዛዥ በመሆን የከፍተኛ የጦር መኮንንነታቸውን ወታደራዊ ግዳጅ ተወጥተዋል። በመቀጠልም ወደ ሐረር ሦስተኛ አንበሳው ክፍለ ጦር በመዛወር የክፍለ ጦሩ ዋና አዛዥ ሆነዋል።



ብርጋዲየር ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ፤

ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ፤ የሦስተኛ አንበሳው ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ ሆነው በሠሩበት አጋጣሚ በኢትዮጵያ የሕዝባዊ አብዮት ንቅናቄ የተፈጠረ በመሆኑና በአራቱም የአገሪቱ አቅጣጫዎች የሚገኙ የጦር ክፍሎች የሠራዊቱን ተወካዮች ወደ ማዕከል እንዲልኩ የለውጡ ሂደት አጠቃላይ ሁኔታ የግድ በሚልበት አጋጣሚ፤ ሦስተኛ አንበሳ ክፍለ ጦርን ወክለው ወደ አዲስ አበባ ለሚያመሩትና በሻለቃ መንግሥቱ ኃይለማርያም እንዲመሩ ለተደረጉት የጦር መኮንኖችና የበታች ሹማምንት አባላት የውሎ አበል አዘው አስፈላጊውን የሽኝት ደብዳቤ ፅፈዋል።

ጄኔራሉ የሦስተኛ አንበሳው ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ ሆነው ሲሰሩ ኋላ ላይ የአገሪቱ ፕሬዚዳንት የሆኑት ኮሌኔል መንግስቱ ሀይለማሪያም የዚሁ ክፍለ ጦር ባልደረባና የስደስተኛ ሜካናይዝድ ብርጌድ የሎጀስቲክ፣ ንብረትና መሳሪያ ግምጃ ቤት አዛዥ ነበሩ። ኮለኔሉ በጄነራል አማን አንዶም ላኪነት ሁለት ግዜ ወደ አሜሪካን አገር አቅንተው ሜሪላንድና ዋሽንግተን ዲሲ መሰረታዊ የመሳሪያ ጥገና ትምህርት የተከታተሉትም በዚህ ወቅት ነበር።

የሦስተኛ ክፍለ ጦር ዋና አዛዥ ሆነው የክፍለ ጦሩን ሠራዊት በመሩበት አጋጣሚ፤ በክፍሉ ከነበሩት ከፍተኛና መስመራዊ መኮንኖች ጋር መልካም የነበረ አስተዳደራዊ፣ የአዛዥና የታዛዥነት ግንኙት የነበራቸው ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን፤ የካቲት 1966 ዓ.ም ብሔራዊ አብዮትን ተከትሎ በሠራዊቱ ውስጥ በተስተዋለው ግልጽ የነበረ የዕዝ ሰንሰለት መዛባት ምክንያት ቅር የተሰኙ በመሆናቸው፤ በወቅቱ የምድር ጦር ሠራዊት ኤታ-ማዦር ሹም ለነበሩት ጄነራል መኮንን ‹‹ሥራዬን በፈቃዴ መልቀቅ እፈልጋለሁ›› የሚል ማመልከቻ አቅርበው፤ በማመልከቻ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ በወቅቱ የኢትዮጵያ ርዕሰ-ብሔር በነበሩት በኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም ትዕዛዝ ተገቢው የአገልግሎት ዘመን መብታቸው ተከብሮ ሠራዊቱን በጡረታ ተሰናብተዋል።

ይህንን በተመለከተ ብርጋዴር ጄኔራል ዋስይሁን ንጋቱ ሲናገሩ ‹‹ ጄኔራሉ እኔ የማዘው መኮንንና የበታች ወታደራዊ ጦር የማይታዘዘኝ ከሆነ የኔ ጄኔራልነት ዋጋ የለውም፤ ስልጣኔንም በገዛ ፍቃዴ እለቃለሁ ብለው ለኮለኔል መንግስቱ ሃይለማሪያም እንዳመለከቱና ጥያቄያቸውም ተቀባይነት አግኝቶ ከነሙሉ ክብራቸው በጡረታ የተሰነባቱ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ጄነራል›› ናቸው ሲሉ ገልፀዋቸዋል።

በግዜው ደርግ ወደ ስልጣን ሲመጣ በርካታ የጦር ጄኔራሎችን ሲያስርና ሲረሽን ብርጋዴር ጄኔራል ጥላሁን ቢሻኔ ‹‹ እጃቸው ከምንም ነገር የፀዳ በመሆኑ፣ ሁኔታውን አይተው በመተንበያቸውና ወደዚህ ምስቅልቅል ሁኔታ ውስጥ ሳይገቡ አስቀድመው በገዛ ፍቃዳቸው ጡረታ በመውጣታቸው ከርሸናው ተርፈዋል እንጂ እርሳቸውም አይቀርላቸውም ነበር›› ይላሉ ብራጋዴር ጄነራል ዋስይሁን ንጋቱ።

ከሁሉ በላይ ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ከጦር አዛዥነታቸው በበለጠ፤ የኢትዮጵያን ሠራዊትና ቤተሰቡን ብሎም ውድ እናት አገራቸውን ያገለገሉት በወታደራዊ የሕክምና ባለሙያነት ተግባር ነው። በዚህ የሕክምና ባለሙያነታቸው የየጦሩን ክፍሎች የጤና ማዕከላት፣ ሆስፒታሎችን በሰው ኃይልና በቁሳቁስ፣ በመድኃኒትና በሕክምና መርጃ መሣሪያዎች ከማደራጀትና የአስተዳደሩን ሥራ ሁሉ በአግባቡና በልዩ የኃላፊነት ስሜት በመምራት እጅግ ምስጉን የሆኑበትን ተግባር አከናውነዋል።

በዚሁ ዘርፍ በጥቅሉ ለሃያ አምስት ዓመታት ስራቸውን በትጋት አከናውነዋል። በዚህም በኢትዮጵያ የምድር ጦር ጠቅላይ መምሪያ ዕዝ ሥር በሚገኘው ዋነኛው የሕክምና መምሪያ ያከናወኗቸው አያሌ ሥራዎች በዋቢነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ከዚሁ የጄኔራሉ ወታደራዊ ህክምና ሞያ አመራርነታቸው ጋር በተያያዘ የቀድሞ የስራ ባልደረባቸው ጄነራል ዋስይሁን ንጋቱ ሲናገሩ ‹‹ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ ከወታደራዊው መስክ ይልቅ በህክምናው ዘርፍ በአዛዥነት ከሃያ አምስት ዓመት በላይ ሰርተዋል። በዚሁ መስክም እነ ጄኔራል ዶክተር ሃይሉ ከፈኔን፣ ዶክተር ጋጋንና ሌሎችንም ወደ ውጪ አገር ጭምር በመላክ እንዲሰለጥኑና የህክምና ሞያ እውቀት እንዲጨብጡ አድርገዋል›› ብለዋል።

‹‹በተጨማሪም ጄነራሉ የምድር ጦር ህክምና መምሪያ ሆነው በቅንነት በማገልገልና የአሁኑ ጦር ኃይሎች ሆስፒታል በሰው ኃይልና በቁሳቁስ እንዲሻሻልም ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። በወታደራዊ ህክምና አመራር ችሎታቸው የተካኑ ሊሆኑ የቻሉትም ጣልያን ከአገሪቱ ወጥቶ እንግሊዞች በኢትዮጵያ በነበሩ ግዜ ከህክምና ባለሞያዎች ጋር ባስተርጓሚነት መስራታቸውና ሃሳብ አመንጪ ስለነበሩ ነው እንጂ ያን ያህል የህክምና እውቀት ኖሯቸው አይደለም። ነገር ግን ደግሞ ወታደራዊ አዛዥነታቸው ህክምናውን ለመምራት ሳይረዳቸው አልቀረም›› ይላሉ ብርጋዴር ጄነራል ዋስይሁን ንጋቱ።

በኢትዮጵያ ቀዳማይ የጦር ክፍሎች ያከናወኗቸው በሳልና እጅግ ፍሬያማ የአስተዳደር፣ የመሪነትና የሕክምና ሙያ አመራር ተግባራት እርሾ የሆኗቸው ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ፤ ከሠራዊቱ ከምስጋና ጋር በጡረታ ከተሰናበቱ በኋላ በነበራቸው ልምድ፣ ችሎታና ብቃት የኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበርን ለስልሳ አራት ዓመታት በነፃ አገልግለዋል። ለወገን ባላቸው የተቆርቋሪነት ስሜትና ተፈጥሮ ባደለቻቸው የሰብዓዊነት ባሕሪ፤ ከኮሎኔል ዶክተር በላይ አበጋዝና ከሌሎችም ቅን የኢትዮጵያ ልጆች ጋር በመሆን የኢትዮጵያ ሕፃናት የልብ ህሙማን ማኅበርን በመመስረትም የዜግነት ግዴታቸውን ተወጥተዋል።

ይኸው የቀይ መስቀል ነፃ አገልግሎታቸውና የበጎ አድራጎት ተሳትፏቸው ከደርግ ውድቀት በኋላ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘም በኋላ ቀጥሏል። አንጋፋው የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር ሰራዊት በቅርቡ እንደገና ሲቋቋምም የእርሳቸው ሚና ከፍተኛ ነበር።

ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ፤ በእሳቸው ሥር በመስመራዊ መኮንንነት ሲሠሩ የነበሩና በስተኋላ ለጄነራልነት ማዕረግ የበቁ፣ እስከ ኮሎኔልነትና ሻለቃነት ማዕረግ የደረሱ አያሌ የጦር አዛዦችና ጀግና፤ ቆራጥ የሠራዊት መሪዎች ዘንድም በእጅጉ የሚደነቁና የሚከበሩም ነበሩ።

በእርሳቸው ስር ተምረው የጄነራልነት ማእረግን ከተቆናጠጡት ውስጥም አንዱ ብርጋዴር ጄነራል ዋስይሁን ንጋቱ ሲሆኑ ‹‹ከእርሳቸው ጋር በቅርበት በመስራቴ ከፍተኛ ኩራት ይሰማኛል፤ ከጅጅጋ ወደ ኤርትራ ተዘዋውሬ የሰራሁትም ከእርሳቸው ጋር ነው። በዚህም ከእርሳቸው ሰፊ እውቀትና ልምድ አግኝቻለሁ›› ይላሉ።

ብርጋዴር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ የ12ኛ ኮርስ ተወዳዳሪ እጩ መኮንን ሆነው ወደውትድርና ዓለም በመቀላቀል ወታደራዊ ስልጠና ወስደው ከኮርሳቸው በመወዳደር ከእጩ መኮንንኖች በወታደራዊ ትምህርት ችሎታቸው አንደኛ በመውጣታቸው ከግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ እጅ የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግና ዲፕሎማ ተቀብለዋል።

በወታደራዊና ህክምና ሞያ አዛዥነት ብቃታቸውም በተለያዩ ግዜያት የሜዳሊያ ተሸላሚ ሆነዋል። ቀይ መስቀልን ለረጅም አመታት በነፃ በማገልገልም የወርቅ ሜዳሊያ ተሸላሚ ለመሆን በቅተዋል። በተጨማሪም ከአለም አቀፍ ቀይ መስቀልና ቀይ ጨረቃ ማህበር የእድሜ ልክ አገልግሎት ሜዳሊያ ሰርተፍኬት ተበርክቶላቸዋል። በበጎ አድራጎት ስራዎች ተሳትፏቸው፤ በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያ ህፃናት ልብ ህሙማን ማህበርን በመመስረት ሂደት ባደረጉት አስተዋፅኦ ከመላው የኢትዮጵያ ህዝብ እውቅናን አግኝተዋል።

ስመ- ጥር፣ አስተዋይና ቀደምት ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ ጄነራል መኮንኖች ውስጥ አንዱ የነበሩት ብርጋዲየር ጄነራል ጥላሁን ቢሻኔ ሐሙስ ሐምሌ ሰባት ቀን 2014 ዓ.ም በ103 አመታቸው በድንገተኛ ህመም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። በዕለተ ዕሁድ ሐምሌ 10 ቀን 2014 ዓ.ም ቤተሰቦቻቸው፣ ወዳጅ ዘመዶቻቸው፣ የቀድሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ባልደረቦች፣ ጄነራሎችና ሌሎች ከፍተኛ መኮንኖች እንደዚሁም በኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና በልብ ሕሙማን መርጃ ማዕከል በከፍተኛ ኃላፊነት፣ አስተባባሪነትና መስራችነት የሚያውቋቸው በርካታ ኢትዮጵያውያን አክባሪ ወገኖቻቸው በተገኙበት በሙሉ ወታደራዊ የማርሽ ባንድ በመካኒሳ ገብረመንፈስ ቅዱስ አቦ ቤተክርስቲያን የቀብር ሥነ-ሥርዓታቸው ተፈፅሟል።

እኚህ አርዓያነታቸው የላቀ ጄነራል ረጅም እድሜ የተጎናፀፉ መንፈሰ-ጠንካራ ኢትዮጵያዊ የነበሩ ሲሆን፤ ከባለቤታቸው ወይዘሮ ትርሲት ቸኮል ጋር ትዳር መስርተው ሰባ አንድ ዓመት ኖረው አምስት ወንድና አንዲት ሴት ልጅ በማፍራት ለቁም-ነገር ያበቁ፤ አስራ አንድ የልጅ ልጆች አያት ለመሆን የታደሉ የአገርና የወገን አውራ ነበሩ።

# ስፖርት



## ትልቅ ትኩረት ያልተሰጠው ታሳቅ ስኬት

ብርሃን ፈይሳ

በመገባደድ ላይ በሚገኘው ዓመት የኢትዮጵያ አትሌቲክስ እጅግ ስኬታማ ጊዜን አሳልፏል። በዚሁ ዓመት በተለያዩ ዓለም አቀፍ መድረኮች የኢትዮጵያ ስም በብርቅዬ አትሌቶቿ አማካኝነት በተደጋጋሚ በክብር ተነስቷል። ከወራት በፊት በሰርቢያ ቤልግሬድ የዓለም የቤት ውስጥ አትሌቲክስ ቻምፒዮና በተመዘገበው አስደማሚ ድል ከአለም ቀዳሚ ሆኖ ያጠናቀቀው የአትሌቲክስ ቡድን፤ ከወራት በኋላ ደግም በኦሪገኑ የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና ሁለተኛ ደረጃን ይዞ ፈጽሟል። በሳምንት ልዩነትም በ20ዓመት በታች የአለም አትሌቲክስ ኢትዮጵያ አስደናቂና ከዚህ ቀደም ከነበረው የላቀ ውጤት በማስመዝገብ ከዓለም ሶስተኛ ሆና ማጠናቀቅ ችላለች። ይህም ሲጠቃለል ኢትዮጵያ በዓመቱ የአፍሪካ አትሌቲክስ ቁንጮ ሆና ማሳለፏን የሚያሳይ ነው። ይህም ስኬት በፌዴሬሽኑ ውስጥ ከአመራር ጋር ተያይዞ አንዳች የተለወጠና ጥሩ መስመር የያዘ ነገር እንዳለ አመላካች ሆኗል።

ወደ ኮሎምቢያ ካሊ ያቀናው የኢትዮጵያ ወጣት አትሌቲክስ ቡድን በውድድሩ ላይ እጅግ አበረታችና በቅርቡ ሁነኛ ተተኪ ሆኖ በዋና ዋና የውድድር መድረኮች ትልቅ ተስፍ እንዳለው የሚያረጋግጥ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል። ከውጤቱ ባለፈም ኢትዮጵያ በታሪክ በየትኛውም የውድድር መድረክ አስመዝግባ የማታውቀውን ከፍተኛ የወርቅ ሜዳሊያ ቁጥር ማሳካት ችሏል። ከዚህ በበለጠ ግን ተስፋ ሰጪ የሆነው በውድድሩ ላይ ተካፋይ ከሆኑት 19 አትሌቶች መካከል 11 የሚሆኑት አትሌቶች የሜዳሊያ




ሰንጠረዥ ውስጥ ሲካተቱ 6 የሚሆኑ አትሌቶች የዲፕሎማ ደረጃ ማግኘት መቻላቸው ነው። ይህም በውድድሩ ከተሳተፉ አትሌቶች ብዛት አኳያ የተገኘው ውጤት ምን ያህል ስኬታማ ወጣት አትሌቶች እየፈሩ መሆኑን በግልጽ አመላካች ነው።

ኢትዮጵያዊያን አትሌቶችን እንደ ኬንያ ካሉ የዘወትር ተቀናቃኞቻቸው በላይ ሆነው ማጠናቀቃቸው አሊያም በሜዳሊያ ሰንጠረዡ አሜሪካ እና ጃማይካን የመሳሰሉ አገራት ተገዳዳሪ በመሆናቸው ብቻም አይደለም። ሩጫና የሜዳ ተግባራትን በመሳሰሉ በርካታ የውድድር አማራጮችን ይዘው የሚፎካከሩ የዓለም አገራትን በጥቂት የውድድር ዓይነቶች (በመካከለኛና ረጅም ርቀት ሩጫዎች ብቻ) ይህንን ውጤት ማስመዝገብ መቻላቸው ትልቅ ስኬት ነው። በተመሳሳይ ከተሳታፊዎቹ ቁጥር አኳያ በሚያገኙት የሜዳሊያ እንዲሁም የዲፕሎማዎች ቁጥር እጅግ ስኬታማ አትሌቶች መሆናቸው ሳይደነቅ አይታለፍም።

ከዚህ ቀደም በነበረው ተሞክሮ ኢትዮጵያ በመሰል ትልልቅ ውድድሮች ላይ በሚኖራት ተሳትፎ ከአትሌቶችና አሰልጣኞች አመራረጥ ጋር በተያያዘ ውዝግቦች ከዝግጅቱ አስቀድሞ ነበር የሚታዩት። በዝግጅት ወቅትም ከአትሌቶች ስነ-ምግባር ጋር በተያያዘ ቅሬታ የሚታይ ሲሆን፤ በውድድር ወቅት የሚመዘገበው ውጤት እንደ አትሌቶች ምንጭነቷ ኢትዮጵያን የሚመጥን አልነበረም ለማለት ያስደፍራል። በዚህም ምክንያት በስፖርት ቤተሰቡ ዘንድ በተደጋጋሚ ቅያሜ ተፈጥሯል።

ከዚህ አንጻር በዓመቱ እየታየ የሚገኘው ስኬት ውዝግብና አለመግባባትን በአንጻራዊነት ያስወገደ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የተገኘ መሆኑ እሙን ነው። ኢትዮጵያዊያን አትሌቶች ከመነሻውም የሚታወቁበት የአብሮነትና በጋራ የመስራት መንፈስ ተመልሶ አትሌቶች በግል ከሚያገኙት ድል ይልቅ የአገራቸውን ክብር ሲያስቀድሙ ታይቷል። ይህም በቡድን ውስጥ ከፍተኛ መከባበር፣ መተሳሰብ እንዲሁም መመካከር እንዳለ አንጸባራቂ ነው። ይህ እንዲመጣ ምክንያት የሆነው ደግሞ የፌዴሬሽኑ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት እንዲሁም አመራሮቹ በጥምረት እየሰሩ ባሉት መልካም ተግባር መሆኑ አያጠያይቅም።

ይህ ይበል የሚያሰኝና አርዓያነት ያለው ተግባር ይሁን እንጂ ይበልጥ ሊተኮርባቸው የሚገቡ ጉዳዮች ላይ ግን አሁንም መስራት አስፈላጊ ነው። ቀዳሚ ሊሆን የሚገባው ደግሞ በአብዛኛዎቹ አፍሪካዊያን አገራት ዘንድ የተለመደው የዕድሜ ጉዳይ ነው። በእድሜ እርከን በሚደረጉ መሰል ውድድሮች ላይ ተካፋይ የሚሆኑ አትሌቶች እድሜ አሁንም አጠራጣሪ ሁኔታ የሚታይበት ነው። ከማሰልጠኛ ተቋማት የሚወጡ ታዳጊዎችን በየጊዜው እግር በእግር በመተካት እንዲሁም እንደየእድሜ እርከናቸው በማሳተፍ ከተጠያቂነት መውጣት ብቻም ሳይሆን ለሌሎች ጀማሪ አትሌቶችም እድል መስጠት አስፈላጊ ነው።

ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ እነዚህ ወጣት አትሌቶች አስፈላጊው ክትትልና ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ነው። ኢትዮጵያ በዚህ ዘርፍ ውጤታማ እንደመሆኗ እንዲሁም ወጣት አትሌቶቹ ቀጣይ የመም ተረካቢዎች እንደመሆናቸው ከውድድር አስቀድሞም ሆነ ከውድድር በኋላ የሚደረግላቸው ድጋፍና ክትትል ዝነኞቹ አትሌቶች ውጤታማ ሲሆኑ እንደሚደረግላቸውም ባይሆን እንኳን ተመጣጣኝ ሊሆን ይገባል። ወጣቶቹን ጀግኖች ዛሬ ማክበር ካልተቻለ አገርን ማስጠራት የሚችሉ ተተኪዎችን ማግኘት አዳጋች እንደሚሆንም ሊዘነጋ አይገባውም።

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም አቶ ዘኪ አብዱላሂ የተሽከርካሪው አይነት ሚኒባስ የሰሌዳ ቁጥር 3-40835ኦሮ የሻንሲው ቁጥር፡- JJ121LK2200037953 የሞተር ቁጥር ፡K-492C012 ሞዴል LXHZZC የሊብሬ ቁጥር 0147205 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር 3-40835 ኦሮ ጠፋብኝ ብለው በ 25/11/2014ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳውን ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የቡራዩ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርት ባለስልጣን**

የባለንብረቱ ስም ምክሩ ይቤ የተሽከርካሪው አይነት ቶዮታ የሰሌዳ ቁጥር 3-70507 ኦሮ የሻንሲው ቁጥር፡JT121JK2200041916 የሞተር ቁጥር ፡ 2KD-1708274 ሞዴል KLH22L-RBMRHW የሊብሬ ቁጥር 0212129 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ የፊት ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው ከክልል ኢፓወመ/125/495/14 እና በ25/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳውን ወድቆ ያገኝ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በፊንፊኔ ዙሪያ በኦሮሚያ ልዩ ዞን የትራንስፖርት ጽ/ቤት**

ንብረትነቱ በአቶ ሚንዳ ቦጋለ የተመዘገበ አይሱዙ ሠሌዳ ቁጥር 03-15711 ኦሮ የሆነ የሻንሲ ቁጥር JAAKP3116787P03389 የሞተር ቁጥር 4HF1-908462 ከላይ የተጠቀሰው አይሱዙ የኋላ ታርጋ ጠፋብን ብለው በ15/09/2014 አመልክቷል፡፡ ታርጋውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የም/ሐረርጌ ዞን ትራንስፖርት ባለሥስጣን**

## በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መ

የባለንብረቱ ስም ሮቤል ምትኩ የሰሌዳ ቁጥር 1-28066 ደ/ህ የተሽከርካሪው አይነት ባጃጅ የሻንሲ ቁጥር MD2A25BY8LWL35369 ሞዴል RE-4S የሞተር ቁጥር AZZWLL01941 ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ 1-28066 ደ/ህ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 1374/ጉዞፖ/15/42 በ13/11/2014 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ታርጋውን/ ሰሌዳውን/ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍርድ ቤት ማሳገጃ ትእዛዝ እንዲያቀርብ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በጉራጌ ዞን ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መመሪያ**

በከሳሽ አቶ ታገሰ ጎቤቦ እና በተከሳሽ አቶ ፀደቀ ታገሰ መካከል ባለው ፍትሐብሔር ክስ ክርክር ጉዳይ ለ19/12/2014 ዓ.ም የተቀረጠ በመሆኑ ተከሳሽ ወደ ሌሞ ወረዳ ፍ/ቤት በቀጠሮ ቀን እንዲቀርቡ ባይቀርቡ ግን በሌሉበት ተሰምቶ ውሳኔ የሚሰጥ መሆኑን የሌሞ ወረዳ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በሀድያ ዞን የሌሞ ወረዳ ፍርድ ቤት**

## አማራ ክልል

ንብረትነቱ የዘይድ አድማሴ ሰሌዳ ቁጥር ኮድ 1-10366 አማ የተሽከርካሪ ሊብሬ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለፅ ሊብሬ ግልባጭ እንዲሰጣቸው በቀን 18/11/ 2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀውናል፡፡ ስለሆነም ይህን ሊብሬ ወድቆ ያገኘ ወይን በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃውን ካላቀረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**የሰሜን ሸዋ ዞን መንገድ ትራንስፖርት መምሪያ**

ንብረትነቱ የተመስገን ጋሻው ኮድ 1-31931 አ.ማ ተሽከርካሪ የኋላ/የፊት/ ሰሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን በመግለጽ ምትክ ሰሌዳ እንዲቀረጽላቸው በ15/11/2014 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠይቀውናል፡፡ ስለሆነም ይህን ሰሌዳ ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል አካል ካለ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ማገጃውን ካላረበ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**ሰ/ሸዋ ዞን መ/ትራ/መምሪያ**

የባለንብረቱ ስም አህመድ ማሩ የሰሌዳ ቁጥር አማ 01-35472 የተሽከርካሪው አይነት ባጃጅ የሻንሲው ቁጥር፡MD-2A25BZ4JWB28342 የሞተር ቁጥር ፡AZZWJC44203 ሞዴል RE-45 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ16/10/2014ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**የማዕከላዊ ጎንደር ዞን መንገድና ትራንስፖርት መምሪያ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ቴድሮስ ሐይሉ ተዘራ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A65141 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር RK110-046161 ሞዴል RK110L-KRH የሞተር ቁጥር 2076174 የሊብሬ ቁጥር 055233 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር /ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው 26/11/2014 አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአተሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃደና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም አቶ ሚካኤል እንዳለ አለሜ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-29171 የተሽከርካሪው አይነት ልዩ ጎታች የሻንሲ ቁጥር wjm53tss00c-013815 ሞዴል 720EH2 የሞተር ቁጥር 821042lx*442-42-427088የሊብሬ ቁጥር 0048885 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 12/11/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአራዳ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ለገሰ ልየው ከበደ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A41222 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAAK-P34HXG7p34157 ሞዴል NPR6SN የሞተር ቁጥር 4HG1-536554 የሊብሬ ቁጥር 469898/469899 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 26/11/2014 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የልደታ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ማፊ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A46670 የተሽከርካሪው አይነት አነስተኛ አውቶቡስ /ከ12 ያነሰ መቀመጫ/ የሻንሲ ቁጥር KMHWH81KBGU806565 ሞዴል GRAND-STAREX የሞተር ቁጥር D4CB-7029364 የሊብሬ ቁጥር 520983/186105 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 26/11/2014 አመልክተዋል፡፡ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት**